# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 041 ጥቅምት 11 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# "ሀገር እየተፈተነች ባለችበት ወቅት ግብራችሁን በታማኝነት በመክፈላችሁ ሽልማቱ ይገባችኋል"

- ሣህለወርቅ ዘውዴ
የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ሀገር እየተፈተነች ባለችበት ወቅት ግብራችሁን በታማኝነት በመክፈላችሁ ሽልማቱ ይገባችኋል ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ለታማኝ ግብር ከፋዮች ምስጋና አቀረቡ። በ2014 በጀት ዓመት የላቀ አፈፃፀም ያስመዘገቡ 400 ታማኝ ግብር ከፋዮች በፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በሽልማት ሥነ ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣ ኢትዮጵያ በጦርነት፣ በመፈናቀል እና በድርቅ እየተፈተነች ባለችበት ወቅት ግብራችሁን በታማኝነት በመክፈላችሁ ሽልማቱ ይገባችኋል ሲሉ ታማኝ ግብር ከፋዮችን አመስግነዋል።

ግብርን በትክክል መክፈል ከማንኛውም የሚሠራ እና የሚያመርት ዜጋ የሚጠበቅ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ግብር በአግባቡ የከፈለ ዜጋ ደግሞ ከመንግሥት መብቱን የመጠቀም መብት አለው ብለዋል፡፡

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሴ በበኩላቸው፣ በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 93 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ከግብር እና ታክስ መሰብሰቡን ተናግረዋል።

በተያዘው ዓመት 450 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ መታቀዱን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ በ2014 በጀት ዓመት በታማኝነት ግብር እየከፈሉ የነበሩ ግብር ከፋዮች ለነበራቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ምሥጋና ይገባቸዋል ብለዋል።



ፎቶ፡ በሃዱሽ አብርሃ

አራተኛው ዙር የፌዴራል ግብር ከፋዮች ዕውቅና እና ሽልማት መርሃ ግብር ሲካሄድ ሽልማት ከተቀበሉት 400 ግብር ከፋዮች መካከል 40 የፕላቲኒየም፣ 120

"ሀገር እየተፈተነች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# "የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትን ስም ለማጠልሸት የሚሰሩ ኃይሎችን በአንድነት መመከት ይገባል"

- ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ሌሊሳ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትህነግ መዳከሙን ሲገነዘቡ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትን ስም በማጠልሸት ከመከላከል ተግባሩ እንዲገታ ለማድረግ የሚጥሩ አንዳንድ የውጭ ጠላቶችና ሚዲያዎቻቸው ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ማድረግ እንደሚገባ የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባል ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ሌሊሳ አሳሰቡ።

የቀድሞ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባል የሆኑት ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ሌሊሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሰሜን ኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት እያደረገ ባለው ራስን ከሽብር ቡድኑ የመከላከል ዘመቻ የሠራዊቱን ስም ለማጠልሸት ከተግባሩ ለማሰናከል የሚሰሩ ኃይሎችን በአንድነት መመከት ይገባል።

እነዚህ ኃይሎች ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ሰላሟና አንድነቷ እንዳትመጣ የሠራዊቱን ስም ለማጠልሸ እየሰሩ ነው ያሉት ሜጀር ጀነራል መርዳሳ፤ እነዚህን የጥፋት ኃይሎች መከላከል የሚቻለው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎችና የጸጥታ አካላት በአንድነት

"የኢትዮጵያ መከላከያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# መንግሥት

## በትግራይ የሰብዓዊ እርዳታን ለማሳለጥ እየሰራ መሆኑ ሕዝቡን ከከፋ ችግር ይታደጋል


**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለትግራይ ክልል የሰብአዊ ድጋፍን በተሳለጠ ሁኔታ ለማዳረስ የጀመረው ስራ ሕዝቡን ከከፋ ችግር ለማላቀቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተጠቆመ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና የዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ ዶክተር ደመቀ ሀጪሶ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሰሞኑን መንግሥት ለትግራይ ክልል ሰብአዊ ድጋፍን ለማዳረስ ማቀዱን ማስታወቁ፤ በአካባቢው ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው የነበሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለከፋ ችግር እንዳይዳረጉ ይረዳል፡፡

"የትግራይ ሕዝብ በአሸባሪው ትሕነግ ምክንያት ከሁለት ዓመታት በላይ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማግኘት አልቻለም፤ ሳይወድ በግድ ወደ ጦርነት እንዲገባ ተደርጓል፤ በመንፈስ፣ በኢኮኖሚና በማሕበራዊ ጉዳዮች

መንግሥት በትግራይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በቡራዩ ከተማ የተገነባውን የባለ ተሰጥኦ ትምህርት ቤት መርቀው ከፈቱ

- ትምህርት ቤቱ አንድ ሺህ ባለተሰጥኦዎችን ማስተናገድ ይችላል

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በ 708 ሚሊዮን 693 ሺህ ብር ወጪ በቡራዩ ከተማ የተገነባውን የልዩ ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት በትናትናው እለት መርቀው ከፈቱ፡፡ ትምህርት ቤቱ አንድ ሺህ ባለ ልዩ ተሰጥኦ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር እንደሚችልም ተጠቅሷል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በቡራዩ ከተማ የተገነባውን የልዩ ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት ትናንት መርቀው ሲከፍቱ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የብሩህ አቅሞችና ተሰጥኦዎች ባለቤት ምድር ናት፡፡ ባለ ተሰጥኦ ታዳጊዎችና ወጣቶች ክህሎታቸውን እያዳበሩ፣ ሀገራቸውን

ጠቅላይ ሚኒስትር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ምክር ቤቱ

## የቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት ለማሻሻል የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ አጸደቀ

ገጽ 3






ፈረንሳይ ለላልይበላ አብያተ ክርስቲያናት ዕድሳት የአምስት ሚሊዮን ዩሮ ድጋፍ አደረገች

ገጽ 3

# የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ውሳኔ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ይከናወናል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የደቡብ ኢትዮጵያ ክልልነት ጥያቄ ላይ የሚደረገው ሕዝበ ውሳኔ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ቦርዱ በተገቢው መንገድ ኃላፊነቱን ይወጣል ሲሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና ሰብሳቢ ብርቱካን ሚደቅሳ ተናገሩ።

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሚገኙ የጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲኦ፣ ኮንሶና፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም የቡርጂ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ባስኬቶ፣ አሌ ልዩ ወረዳዎች የሚካሄደውን ሕዝበ ውሣኔ ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚከናወን ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አስታውቋል።

የቦርዱ ዋና ሰብሳቢ ብርቱካን ሚደቅሳ በሰጡት መግለጫ፤ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከጊዜ ወደጊዜ አሰራሩንና ደረጃውን እያሳደገ በመሆኑ ሕዝበ ውሳኔውም በተሻለ ሁኔታ እንዲከናወን ያደርጋል ብለዋል።

ሕዝበ ውሳኔው ሰላማዊ፣ ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ቦርዱ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ይወጣል ሲሉ ዋና ሰብሳቢዋ ተናግረዋል።

ሕዝበ ውሳኔው ነጻና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ከሚደረጉ ዝግጅቶች መካከል የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ምልመላ ሥራ እንደሚገኝበት ብርቱካን ሚደቅሳ ገልጸዋል።

ለምልመላ በሚቀርቡ እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚ ላይ ቅሬታ አለኝ ያለ አካል ሪፖርት ማድረግ የሚችልበት አሰራር መዘርጋቱን አስረድተዋል። ከዚህ ቀደም በፖለቲካ ፓርቲ፣ በሲቪክ ማህበራትና በተቋማት ካልሆነ በቀር በግለሰብ ደረጃ በምርጫ አስፈጻሚዎች ላይ ቅሬታ የሚቀርብበት አካሄድ እንዳልነበር አስታውሰዋል።

በሕዝብ ውሳኔው ላይ ግን በምርጫ አስፈጻሚዎች ሥነምግባርና ገለልተኝነት ላይ ጥያቄ አለኝ የሚል ማንኛውም ግለሰብ በማስረጃ በተደረፈ መንገድ ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚችልም ጠቁመዋል።

በእስካሁኑ የአስፈጻሚዎች ምልመላ በስድስተኛው አገራዊ ምርጫ የተሳተፉ ዘጠኝ ሺህ አስፈጻሚዎች በደቡብ ኢትዮጵያ የሕዝበ ውሳኔ ላይ በድጋሚ ለማገልገል ፍቃደኛ መሆናቸውን ገልጸዋል ያሉት የቦርዱ ሰብሳቢ፤ በአጠቃላይ 18 ሺህ 750 የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች እንደሚያስፈልጉ አስረድተዋል።

ቀሪዎቹን የምርጫ አስፈጻሚዎች ለመመልመል ቦርዱ የቅጥር ማስታወቂያ እንደሚወጣ ገልጸዋል። እንደ ብርቱካን ሚደቅሳ ከሆነ፤ ከምልመላ ሥራው ባለፈ ለሕዝበ ውሳኔው መሳካት የሚረዱ የውይይት መድረኮች ከሲቪክና ፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ ከማህበረሰቡና ከሚመለከታቸው የጸጥታ አካላት ጋር ተካሂደዋል።

በእስካሁኑ የዝግጅት ሥራ የሕዝበ ውሳኔው ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት በአርባምንጭ ከተማ ተቋቁሟል። በዞንና በልዩ ወረዳዎች መከፈት ያለባቸው 11 ጽህፈት ቤቶች እስከትናንትናው ዕለት ድረስ



ብርቱካን ሚደቅሳ

አልተከፈቱም ብለዋል።

ለዚህ ደግሞ የየአካባቢው አስተዳደሮች በወቅቱ አስፈላጊውን ትብብር ባለማድረጋቸው የተፈጠረ በመሆኑ አስተዳደሮቹ አስፈላጊውን ትብብር በወቅት እንዲያደርጉ ዋና ሰብሳቢዋ ጥሪ አቅርበዋል።

በደቡብ ብሔሮች ብሔርብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሚገኙ ስድስት ዞኖች እንዲሁም አምስት ልዩ ወረዳዎች የሚገኙ ዜጎች ደቡብ ኢትዮጵያ በሚል አዲስ ክልል እንመስርት፤ አልያም በነበረው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልልነት እንቀጥል በሚል ሕዝብ ውሳኔውን ያደርጋሉ።

ለሕዝበ ውሳኔው በመራጭነት ሊመዘገቡ የሚችሉ ግምታዊ መራጮች ሶስት ሚሊዮን 106 ሺህ 585 ሠዎች መሆናቸውን ቦርዱ አሳውቋል። ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለሚያካሂደው ሕዝበ ውሣኔ ማስፈጸሚያ 410 ነጥብ 1 ሚሊዮን ብር ከመንግሥት ተፈቅዷል።



# መንግሥት በትግራይ ክልል ሰብዓዊ እርዳታን በተሳለጠ መንገድ ለማዳረስ በቂ ዝግጅት ማድረጉን አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል ከአሸባሪው ሕወሓት ቡድን ነጻ በወጡ አካባቢዎች ሰብዓዊ እርዳታ በተሣለጠ መንገድ እንዲደርስ በቂ ዝግጅት መደረጉን ለሰብዓዊ ድጋፍ የተዋቀረው ኮሚቴ አስታወቀ።

ሰብዓዊ እርዳታን በተቀናጀ፣ በተፋጠነ እና በተሣለጠ መልኩ ማድረስ የመንግሥት ፅኑ አቋም መሆኑም ተገልጿል።

ከአሸባሪው ቡድን ነጻ በወጡ አካባቢዎች ሰብዓዊ እርዳታ በተሣለጠ መንገድ እንዲደርስ ባለድርሻ አካላት በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ለሰብዓዊ ድጋፍ የተዋቀረው ኮሚቴ ገለጸ።

የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦትን ለማሳለጥ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ ከሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ ፌዴራል ፖሊስ እና የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ ገብቷል።

የኮሚቴው ሰብሳቢ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን፤ መከላከያ ሠራዊት በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ሰብዓዊ እርዳታውን በተሣለጠ መልኩ ለማድረስ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱንና ወደ ተግባር መግባቱን ገልጸዋል።

ኮሚቴው ዝግጅቱን አስመልክቶ ባደረገው ውይይት ከአሸባሪው ነጻ በወጡ የትግራይ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ሰብዓዊ እርዳታ እንዲደርስ ባለድርሻ አካላት በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውንም አረጋግጧል።

የሽሬ አውሮፕላን ማረፊያን ተጠቅሞ ዕርዳታ ማድረስን እንደሚጨምር የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትርና አምባሳደር ሬድዋን ተናግረዋል።

ሰብዓዊ እርዳታን በተቀናጀ፣ በተፋጠነና በተሣለጠ መንገድ ማድረስ የመንግሥት ፅኑ አቋም እንደሆነም ገልጸዋል።

ለዚህም ኮሚቴው በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን ለይቶ በቅንጅት እንደሚሰራ ተናግረዋል። ነጻ በወጡ አካባቢዎች የመንግሥት መዋቅሩን መልሶ በማደራጀት የተቀናጀ የሰብዓዊ እርዳታ ተደራሽ እንዲሆን ይሰራል ብለዋል።

መንግሥት ያስቀመጠው አቅጣጫ ተገቢና ትክክለኛ መሆኑን ያመለከቱት የኮሚቴው አባላት፣ ውሳኔውን ለመተግበር በየዘርፉ የሚመለከታቸው አካላት በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውንም አስረድተዋል።

በዚህም ከአሸባሪው ሕወሓት ነፃ በወጡ አካባቢዎች የእርዳታ አቅርቦቱ ሳይስተጓጎል ማድረስ በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ በቅንጅት እንደሚሰሩም መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

መንግሥት ከሰብአዊ የእርዳታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ሰብአዊ ዕርዳታ የሚደርስባቸውን መንገዶች እያስፋፋ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በትላንትናው እለት መግለጹ ይታወቃል።

# በክልሉ ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ የድርሻቸውን እንደሚወጡ የሀገር ሽማግሌዎች አረጋገጡ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አስተማማኝና ዘላቂ ሠላም ለማረጋገጥ እየተደረገ ላለው ሁሉን አቀፍ ጥረት ስኬት የሚጠበቅባቸውን እንደሚወጡ የክልሉ የሀገር ሽማግሌዎች አስታወቁ።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሕገ-ወጥ መንገድ ታጥቆ ሲንቀሳቀስ የነበረው የጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጉህዴን) በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሠላም ለመንቀሳቀስ ከክልሉ መንግሥት ጋር የሠላም ስምምነት መፈራሙን ኢዜአ ዘግቧል።

በስምምነት ሥነ-ሥርዓቱ ወቅት የክልሉ ሀገር ሽማግሌዎች፤ በክልሉ አስተማማኝና ዘላቂ ሠላም ለማረጋገጥ እየተደረገ ላለው ሁሉን አቀፍ ጥረት የሚጠበቅባቸውን እንደሚወጡ አረጋግጠዋል።

ከሀገር ሽማግሌዎቹ መካከል የቀድሞው የክልሉ ከፍተኛ አመራር አቶ አብዱልማሙድ ኢብራሂም፤ “ከሀገራዊ ለውጥ ወዲህ የተገኘውን ነፃነት ተጠቅመን የህዝባችንን ፍላጎት ለማሟላት ተደማምጠን መስራት የግድ ነው” ብለዋል።

የተደረሰው ስምምት ችግሮቻቸውን በውይይትና በመነጋገር መፍታት እንደሚችሉ በተጨባጭ ያሳየ መሆኑን ጠቅሰው፤ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ትዕግስትን የተላበሰ ውሳኔ በመስጠታቸው አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

ይህን ተሞክሮ ተጠቅመን ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት መስራት ይጠበቅብናል ያሉት አቶ አብዱልማሙድ፤ እሳቸውም የክልሉን ሠላም አስጠብቆ ለማስቀጥል እየተደረገ ያለውን ጥረት በመደገፍ የድርሻቸውን እንደሚወጡ አስታውቀዋል።

ሌላው የሀገር ሽማግሌ አቶ ገለታ ጋጋ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ የክልሉን ሠላም ለመመለስ የተደረገው ጥረት ውጤት በመሆኑ መደሰታቸውን ገልጸዋል።

ያለንበት ዘመን ችግሮቻችንን በጠመንጃ ሳይሆን በመነጋገር ብቻ የምንፈታበት ነው ያሉት አቶ ገለታ፤ ለዚህም መፍትሄው ሁሉም በሰከነ አግባብ እንዲመራ መክረዋል። አቶ ገለታ አክለውም ለክልሉ ሠላምና ደህንነት መጠበቅም የሚጠበቅባቸውን እንደሚወጡም አረጋግጠዋል።

የክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሃሰን ስምምነቱ የክልሉን ሕዝብ ጥቅም እና ሕገ-መንግሥቱን መሰረት አድርጎ የተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ በኋላ ችግሮች ቢያጋጥሙ እንኳን በሠላማዊ መንገድ ብቻ መፍታት እንደሚገባ አመልክተው፤ ከስምምነቱን ውጪ ሠላምን ለማደፍረስ የሚደረግ ማንኛውም ድርጊት ተቀባይነት አይኖራቸውም ብለዋል።

የክልሉ የሀገር ሽማግሌዎች የሠላም ስምምነቱ እንዲሳካ ላበረከቱት አስተዋጽኦ አመስግነው፤ በፀጥታ ችግር የተጎዳውን ሕብረተሰብ አስተማማኝ ሠላምን ዘላቂ በማድረግ ጥያቄውን የመመለስ ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል።

የክልሉ የሀገር ሽማግሌዎች ድጋፍና ትብብራቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉም ርዕሰ-መስተዳድሩ ጠይቀዋል። የንቅናቄው አባላትም ሆኑ ሌሎችም የጉሙዝ ወጣቶች ለሠላም ስምምነቱ ተግባራዊነት የበኩላቸውን መወጣት እንዳባቸው አቶ አሻድሊ አስገንዝበዋል።

የጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጉህዴን) ሊቀመንበር ግራኝ ጉደታ፤ በበኩላቸው በገጠሙን ችግሮች ላይ በአግባቡ ተወያይተን አለመፍታታችን በማህበረሰቡ ላይ ጉዳት አስከትሏል ሲሉ ገልጸዋል።

የክልሉን ሠላም በማጠናከር ሐረብረተሰቡ የተፈጥሮ ሀብቱን በሚገባ ተጠቅሞ ከድህነት እንዲወጣ ከክልሉ መንግሥት፣ ከሁሉም ማህበረሰብና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ እንሠራለን ብለዋል።

በየደረጃው የሚገኙ የንቅናቄው አባላት ስምምነቱን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ እንደሚደረግም አስታውቀዋል። ለስምምነቱ ተግባራዊነት ከልብ እንሰራለን ያሉት ሊቀመንበሩ፤ ለስምምነቱ ስኬታማነት አስተዋጽኦ ያደረጉትን ሁሉ አመስግነዋል።

የሠላም ስምምነቱን ከክልሉ መንግሥትና ከንቅናቄው በተጨማሪ የክልሉ ኮማንድ ፖስት አስተባባሪ ሜጀር ጀኔራል ከፍያለው አምዴ እና ተሳታፊ የሀገር ሽማግሌዎችም ፈርመዋል።

ዜና



አቶ ታገሰ ጫፎ

## ምክር ቤቱ የቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት ለማሻሻል የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ አጸደቀ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ስብሰባው የቋሚ ኮሚቴዎችን ስራ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀትን ለማሻሻል የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ አጸደቀ። ምክር ቤቱ ሶስት ረቂቅ አዋጆች ላይ ተወያይቶ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ የውሳኔ ሃሳቡን አስመልክቶ እንዳብራሩት፤ የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት ራሱን በቻለ ውሳኔ እየተመራ የሚሄድበት በምክር ቤቱ የአባላትና የአሰራር፣ የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 ላይ ተደንግጓል። 6ኛውን ሀገራዊ ምርጫ ተከትሎ አዲስ ምክር ቤት በመመስረት አገራዊ ሁኔታውንና የመንግሥት አደረጃጀትና የትኩረት አቅጣጫውን መነሻ ያደረገ የቋሚ ኮሚቴዎች የአደረጃጀት ማሻሻያ ተደርጎ ውሳኔ ቁጥር 3/2014 ሆኖ መጽደቁን አስታውሰዋል።

በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የስራ ዘመን አንደኛ የስራ ዓመት የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት በተግባር ሲታይ የነበረው አፈጻጸም ውጤታማ ነበር። ነገር ግን በተግባር በአፈጻጸም ወቅት በአንዳንድ ቋሚ ኮሚቴዎች ላይ የነበረውን ጫና ለመቀነስ፣ የክትትልና የቁጥጥር ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ የሕግ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴን እንዲሁም የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴን እንደገና ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን አፈ ጉባኤው ለምክር ቤቱ አብራርተዋል።

የቋሚ ኮሚቴዎችን እንደገና የማደራጀትና ማሻሻል አስፈላጊነት የአደረጃጀት ተግባራዊነቱን በላቀ የውጤታማነት ደረጃ ለማከናወን እንዲቻል ታስቦ የሚቀየስ ስልት ነው። ስለሆነም ነባራዊ ሁኔታውንና በአፈጻጸም የታዩ ተግዳሮቶችን፣ ጉድለቶችን ለመቅረፍ እንዲያስችል ማሻሻያ ማድረግ ይጠይቃል ብለዋል።

አፈ ጉባኤው፤ 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትን፣ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ፣ የ2014 እቅድ ትኩረቶች እንዲሁም የምክር ቤቱን የክትትልና የቁጥጥር መመዘኛ መስፈርትና የምክር ቤቱን የ2014 እቅድ መሰረት በማድረግ በውሳኔ ቁጥር 3/2014 መጽደቁ ይታወሳል። የተሻሻለው የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት ከ2014 ከነበረው የቋሚ ኮሚቴዎች አፈጻጸም አንጻር ሲታይ ውጤታማ ቢሆንም በአፈጻጸም ወቅት ከነበሩ ችግሮች መካከል የሕግ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በንጽጽር ሲታይ የሚከታተላቸው ተቋማት ብዛት በቋሚ ኮሚቴዎች ላይ የስራ ጫና መፈጠሩ ለመሻሻሉ አንዱ ምክንያት መሆኑን አብራርተዋል።

የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትሩ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ የረቂቅ አዋጆችን አስፈላጊነት ለምክር ቤቱ አባላት በሰጡት ማብራሪያ፤ እስካሁን ከነበሩ የስራ እንቅስቃሴዎች መልካም ልምዶችን በማጎልበት የታዩ ጉድለቶችን በመሙላት በተያዘው ዓመት አፈጻጸምን ከፍ ወዳለ ደረጃ ማድረስ ያስፈልጋል። ማሻሻያው የክትትልና የቀጥጥር ስራውን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በሚደረገው ሂደት ላይ የተቋማት ብዛት አሉታዊ ጫና ስላለው ማሻሻያ ማድረጉ ወሳኝ ነው። በተጨማሪም የቋሚ ኮሚቴዎች ቁጥር ከ15 እስከ 25 ከፍ ተደርጓል ብለዋል።

ከውሳኔው ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ ውሳኔ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት ለማሻሻል የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ውሳኔ ቁጥር 1/2015 ሆኖ በሙሉ ድምጽ ጸድቋል።

ምክር ቤቱ በትናንትናው ውሎው ከአንደኛ መደበኛ ስብሰባው የተሸጋገሩ የዕጽዋት ዘር ለመደንገግ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ፣ የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰንና የዲጅታል መታወቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ በምክር ቤት አባላት የተሰጡ ዝርዝር አስተያቶችንና ጥያቄዎችን ጨምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

# ፈረንሳይ ለላልይበላ አብያተ ክርስቲያናት ዕድሳት የአምስት ሚሊዮን ዩሮ ድጋፍ አደረገች

**ዘላለም ግዛው**




አዲስ አበባ፡- ፈረንሳይ የላልይበላ አብያተ ክርስቲያናትን ከጉዳት ለመጠበቅ፣ ለማደስ እና ለማልማት የሚያስችል የአምስት ሚሊዮን ዩሮ (የ260 ሚሊዮን ብር) ድጋፍ አደረገች፡፡

የድጋፍ ስምምነቱን በኢትዮጵያ በኩል የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰመሪታ ሰዋሰው እና በፈረንሳይ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሬሚ ማሬሽ ትናንት ተፈራርመዋል፡፡

ስምምነቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከአራት ዓመታት በፊት ከፈረንሳይ ፕሬዚደንት ኢማኑኤል ማክሮን ጋር በተወያዩበት ወቅት ሁለቱ አገራት በቅርስ ጥበቃ ለመተባበር መግባባት ላይ በደረሱበት መሰረት የሚተገበር የፕሮጀክት አካል መሆኑ ተገልጿል፡፡

በስምምነቱ ወቅት ወይዘሮ ሰመሪታ እንደተናገሩት፤ ድጋፉ የፈረሱና የተጎዱ የላልይበላ አብያተ ክርስቲያናትን ለመጠገን ህንጻውን ባለበት ሁኔታ እንዲቆይ ለመንከባከብ የሚያስችል ነው፡፡

ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር የተለያዩ ስራዎች እንደሚሰሩ በመጠቆምም፤ ፈረንሳይ በቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ልምድ ካላቸው አገራት ተርታ የሚመደብና በርካታ የቱሪስቶች ፍሰት ያሏት አገር መሆኗን ተናግረዋል፡፡ የባህልና የታሪካዊ ስፍራዎችን በማስጎብኘት እንደምትታወቅም አመልክተዋል፡፡

ድጋፉ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ቅርሶች በማሳደግ እና በማልማት የቱሪስቶችን ፍሰት እንዲጨምር የሚያደርግ፣ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ የሚያሳድግ፣ ለአካባቢው ማሕበረሰብ ተጨማሪ የሥራ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን እና የግሉን ዘርፍ እንደሚያበረታታ ነው የጠቆሙት፡፡

ኢትዮጵያ ፈረንሳይ በቱሪዝም እና በቅርስ ጥበቃ ዘርፍ ያላትን ልምድ በመቅሰም የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብት የበለጠ ለመጠበቅና ለማጎልበት ትሰራለች ያሉት ወይዘሮ ሰመሪታ፤ ከዚህ ጋር ተዛማጅ የሆኑና በብሄራዊ ቤተ መንግሥቱ ዙሪያ የሚሰሩ ሙዚየሞችን ስራ ይደግፋሉ ብለዋል፡፡

ፈረንሳይ ከዚህ ባሻገርም፤ በኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ በሃይል እና በምግብ ዋስትና ዙሪያም የሚያደርጓቸው በርካታ ድጋፎች መኖራቸውንም ነው የተናገሩት፡፡

ረጅም ጊዜ የቆየው የሁለቱ አገራት መልካም ግንኙነት እና ትብብር በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡትን የላልይበላ አብያተ ክርስቲያናት የደረሰባቸውን ጉዳት ለመጠገን እና ለማልማት ባሳዩት ትብብር ተጠናክሮ መቀጠሉንም አመልክተዋል፡፡


ትብብሩ የላልይበላ አብያተ ክርስቲያናትን በመጠበቅና በማልማት ቅርሶቹ ከአካባቢው ማሕበረሰብ ጋር ተስማሚ፣ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል እና የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣንን አቅም ለመገንባት የሚያግዝ መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

የፈረንሳይ አምባሳደር ሬሚ ማሬሽ እንደገለጹት፤ ድጋፉ በዓለም ቅርስነት በዩኔስኮ የተመዘገበው የላልይበላ አብያተ ክርስቲያናትን ከጉዳት በመጠበቅ፣ በማደስ እና በማልማት ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው፡፡

አጠቃላይ በአካባቢው የቱሪዝም ፍሰትን በማሳደግ እና የሥራ ዕድል በመፍጠር አካባቢውን የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ረጅም ዓመታት የዘለቀው የዲፕሎማሲ ግንኙነት በባህልና በቅርሶች ጥበቃ ዘርፍ ተጠናክሮ እንደቀጠለም አምባሳደር ሬሚ ማሬሽ ተናግረዋል፡፡

# የሳይንስ ሙዚየሙ የፈጠራ ስራዎች በፍጥነት ወደ ቴክኖሎጂ እንዲቀየሩ ያደርጋል

**ገመቹ ከድር**



ግብርና ስራን የሚያግዝ ድሮን

አዲስ አበባ፡- በቅርቡ ተመርቆ ለዕይታ ክፍት የተደረገው የሳይንስ ሙዚየም በተለያዩ ደረጃዎች የሚፈጠሩ የፈጠራ ስራዎች በፍጥነት ወደ ቴክኖሎጂ እንዲቀየሩ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው በፈጠራ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ተናገሩ።

ድሮን ፈጠራ ስራ ላይ የተሰማሩት የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ መምህር አማኑኤል ባልቻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሳይንስ ሙዚየም በፈጠራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ስራ በፍጥነት ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ቴክኖሎጂ እንዲቀየር ያደርጋል። ቴክኖሎጂን ያለፈጠራ እውን ማድረግ አይቻልም፣ ሀገር የምትፈልገውን ቴክኖሎጂ ለማስገኘት ፈጠራ ስራ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

እንደ መምህር አማኑኤል ገለጻ፤ ዓለም በሰው አእምሮ የተፈጠሩ ነገሮችን በማበልጸግ የማህበረሰቡን ችግሮች መፍታት ወደሚያስችል ቴክኖሎጂ በማሸጋገር ላይ ትገኛለች። እንደ ሀገር የሚያስፈልጉንን ቴክኖሎጂዎች ለማሳደግም እሳቸው ከዘመኑ ቴክሎጂዎች አንዱ በሆነው የድሮን ቴክኖሎጂ ላይ ተሰማርተዋል። እስከ አሁን ድረስ በሰሩት የፈጠራ ስራ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ዘጠኝ ድሮኖች መፍጠራቸውንም ገልጸዋል።

በፈጠራ ስራቸው ከተሰሩ ድሮኖች በአብዛኛው በግብርና ዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያገለግሉ ናቸው ያሉት መምህር አማኑኤል፣ 500 ሚሊ ሊትር ኬሚካል ይዞ መብረር የሚችል ድሮን መፍጠር እንደቻሉ ገልጸዋል።

በጤና ዘርፍ የደም እጥረት ባለበት ቦታ በፍጥነት በመድረስ፣ ትላልቅ ህንጻዎች በሚገኙበት አካባቢ በእሳት አደጋ ማጥፊያ ኬሚካሎችን በፍጥነት በማድረስ አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ ድሮኖች እንደሚገኙበት ገልጸዋል።

ኮምፒውተር ኢንጅነሪግ ምሩቅና ያለ ክፍያ አገልግሎት የሚሰጥ ስልክ ፈጠራ ባለቤት የሆኑት ኤስራኤል ቤለማ በበኩላቸው ሳይንስ ሙዚየም በፈጠራ ስራ ላይ ተሰማርተው በመስራት ላይ ለሚገኙ የፈጠራ ባለሙያዎች ስራቸው በፍጥነት እንዲታወቅ በማድረግ ወደ ቴክኖሎጂ የሚደረገውን ጉዞ ያፋጥናል ብለዋል።

ያለ ክፍያ አገልግሎት የሚሰጥ ስልክ ከፈጠሩ በኋላ ባለችበት ቦታ መረጃ መስጠት የሚያስችል የመኪና ደህንነት ፈጠራን መፍጠራቸውን ገልጸው እስከአሁን ድረስ በሰሩት ፈጠራ ስራ ሦስት የአዕምሮ ፈጠራ ባለቤትነት መብት (patente right ) እና 36 ዓለም አቀፋዊ ምስክር ወረቀት በማግኘት 'Young gneiss Ethiopian the first Africa " በመባል ዕውቅና አገኝቷል።

በአገኙት እውቅና የተለያዩ ልምዶችን በመቅሰም ከዩኒቨርሲቲ የወጡ ስራ ለሌላቸው ወጣቶች በኮምፒዩተር ጥገና ፣ በሶፍትዌር ስራ እና በተያያዙ ፈጠራ ስራ ፕሮጀክቶች ስልጠና በመስጠት ለ10 ወጣቶች የስራ ዕድል ፈጥረዋል።

በተመሳሳይም ከተሞችን ስማርት በማድረግ በሱሉልታ በጣፎ ከተማ ወደ ስማርት ከተማ ለማስቀየር የሚያስችሉ ድጋፎችን በመስጠት ላይ እንደሚገኙ ጠቅሰው በፈጠራ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በትኩረት በሳይንስ ሙዚየሙ እንዲጠቀሙ ጥሪ አቅርበዋል።

በፈጠራ ስራ ላይ ተሰማርቶ በመስራት ላይ የሚገኙት አቶ ሐምባ አብዲሳ ዓለማችን በሰው ጉልበት የሚሰሩ ስራዎችን ወደ ዲጅታል ለመቀየር እየተንቀሳቀሰች መሆኑን ጠቅሰዉ እንደ ሀገር ወደ ዲጅታል የሚደረገውን ጉዞ ለመቀላቀል ሳይንስ ሙዚየሙ በፈጠራ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን የሚያበረታታ ነው ብለዋል።

ቀጣይ ትውልድ በቲዮሪ የሰማውን በተግባር በማየት ወደ ተክኖሎጂ የሚያደርሰውን ፈጠራ ስራ በማጠናከር ለሀገሪቱ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎች ለመፍጠር በር የሚከፍት ጅማሮ ነው በማለት ገልጸዋል።

ዜና

# በአሸባሪው ትህነግ የወደመውን የባቡር ፕሮጀክት ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሰራ ነው



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ባሕር ዳር፡- በአሸባሪው ትህነግ ጉዳት፣ ውድመት እና ዘረፋ የደረሰበትን የአዋሽ-ወልዲያ-ሀራ ገበያ የባቡር ፕሮጀክትን ወደ ሥራ ለማስገባት እንቅስቃሴ መጀመሩን የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን አስታውቋል።

የባቡር መስመሩ የሽብር ቡድኑ በከፈተው ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ፕሮጀክቱን እያከናወነ ያለው ተቋራጭ ለተበላሹ፣ ለተዘረፉት እና ለወደሙ ንብረቶቹ ካሣ መጠየቁን ኮርፖሬሽኑ አስታውቋል።

ኮርፖሬሽኑ የተቋራጩን ጥያቄ ለመመለስ ብሎም አጠቃላይ የባቡር ሥራውን ለማስቀጠል ቅርንጫፎችን በመክፈት እና የጠፉ እና የወደሙ ንብረቶችን በመለየት በየአካባቢው ጥናት እያደረገ መሆኑን ትናንት በሰጠው መግለጫ አስታውቋል።

270 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው የአዋሽ-ኮምቦልቻ የባቡር መስመር በአሸባሪ ቡድኑ በከፋ ሁኔታ ጉዳት እንደደረሰበት ተገልጿል። የአዋሽ-ኮምቦልቻ የባቡር መስመር 99 በመቶ ከ3 ዓመት በፊት ተጠናቆ የነበረ፣ ነገር ግን በኃይል እጥረት ምክንያት የዘገየ መሆኑ ተጠቅሷል።

እስካሁን በተደረገው ጥናት የአዋሽ-ኮምቦልቻ የባቡር መስመር በአሸባሪው ትህነግ ቡድን ከፍተኛ ዘረፋ፣ ውድመት እና ጉዳት እንደደረሰበት ተገልጿል። 50 በመቶ ተጠናቅቆ የነበረው ከወልዲያ መቀሌ የሚወስደው የባቡር መስመርም ጉዳት እንደደረሰበት በጋዜጣዊ መግለጫው ተጠቅሷል ሲል የዘገበው የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ነው፡፡

የደረሰውን ውድመት አስተካክሎ ወደ ሥራ እንዴት መግባት ይቻላል በሚለው ላይ ጥናቶችን በማካሄድ በየአካባቢው ያሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን እየከፈቱ ዳግም ሥራ ለማስጀመር በንግግር ላይ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ገልጿል።



ዶክተር ደመቀ ሀጪሶ

# መንግሥት...

እንዲገለል ሆኗል" ያሉት ዶክተር ደመቀ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደማንኛውም ሉዓላዊ ሀገርና ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ሕዝብ ትግራዋይ መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እርዳታዎችን በተገቢው ሁኔታ እንዲጠቀሙ መንግሥት የመስራትና ለዚህ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነት እንዳለበት አንስተዋል።

ከዚህ በፊት አሸባሪው ትሕነግ ተቆጣጥሮ በቆየባቸው አካባቢዎች የሰብዓዊ እርዳታዎች የሚገቡበት ሁኔታ ቢኖርም ለተጎጂ ዜጎች ግን የሚደርሰው የሰብአዊ እርዳታ ለወታደራዊ አገልግሎቶች ይውል እንደነበር አስታውሰዋል።

በጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖሩ ተፈናቃዮችና ተጎጂዎችም መሰረታዊ የሰብዓዊ አገልግሎቶችን ሊያገኙ አለመቻላቸውን የጠቀሱት ምሁሩ፤ አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍ ለማድረግ መዘጋጀቱ ችግሩን ለማቃለል አይነተኛ መፍትሄ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል ሀገር ሉዓላዊነቷ ተጠብቆ በጦርነት ቀጠና ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ከዚህ በፊት አግኝተው የማያውቁትን ሰብአዊ እርዳታ ለማከፋፈል ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርም ገልጸዋል።

መንግሥት በራሱ ድጋፍ የሚያደርስ ከሆነ ከዚህ በኋላ የሕዝቡን እርዳታ የሚሻማ፣ የሚያባክን እንዲሁም ለተለየ ዓላማ የሚያውል ኃይል ሊኖር እንደማይችልም ተናግረዋል።

የሰብዓዊ እርዳታ ጭነው ወደ ክልሉ የገቡ ተሽከርካሪዎች በአግባቡ እንዲመለሱ፣ የእርዳታ ቁሳቁሶችም ለተረጂዎች በአግባቡ እንዲደርሱ እና እርዳታውን ጭነው የሚጓጉዙ ሰራተኞች ደህንነትም በአግባቡ እንደሚጠበቅ የሚያደርግ መሆኑንም ገልጸዋል።

ዓለም አቀፍ ተቋማት የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትን ባከበረ መልኩ መንቀሳቀስ እንዳለባቸውና በየትኛውም የሰብዓዊ አገልግሎቶች ላይ እሰራለሁ የሚል አካል ከፖለቲካ ዓላማ እጁን በመሰብሰብ ተጎጂ ማህበረሰቡን ብቻ ማገልገል እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል።

የትግራይ ሕዝብ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን አካል በቂ ጊዜ በመውሰድ የለየ በመሆኑ ከዚህ በፊት የተፈጠሩ ክፍተቶችን በማረም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር አብሮ መስራት እንዳለበት የጠቀሱት ዶክተር ደመቀ፤ ማሕበረሰቡ ወንጀለኞችን በጋራ በመከላከል ተባብሮ መስራት ይጠበቅበታልም ብለዋል።

# "የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትን ስም...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

መንፈስ ሲሰሩ ነው ብለዋል፡፡

ዘር እየመረጡ የሚገድሉና የኢትዮጵያን ህልውና የማይፈልጉ የጥፋት ኃይሎች ኢትዮጵያ ሰላም እንዳትሆን ስጋቶች ናቸው ያሉት ሜጀር ጀነራል መርዳሳ፤ እነዚህን የጥፋት ኃይሎች መከላከል የምንችለው እያንዳንዱ ዜጋ ከጸጥታ አካሎች ጋር ተቀናጅቶ መስራት ሲችል እንደሆነ አመልክተዋል።

እያንዳንዱ ዜጋ ከጸጥታ አካሎች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ከሆነና ሽብር ቡድኑን እኩይ ተግባር ከስር ከስር እያጋለጠ ከሄደ የሠራዊቱን ስም ለማጠልሸት የሚያደርገው ጥረት ያልተገባና ሀሰተኛ መረጃ እንደሆነ በቀላሉ ማወቅ ይቻላል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ገለፃ፤ ሕወሓት ሥልጣን ከመያዙ በፊት ጀምሮ የውሸት ፕሮፓጋንዳ መንዛት፣ የሠራዊቱን ስም ማጠልሸት እና ከውጭ ጠላቶች ጋር በማበር ሀገርን ለማፍረስ መንቀሳቀስ የኖረበት እና ያደገበት ባህርይው ነው፡፡

ሌላው ሕወሓት ከቀድሞ ሠራዊት ጋር ጦርነት በሚያደግበት ወቅት ለሠራዊቱ የማይመጥን መጥፎ ስም በመስጠት ሕዝቡ ለወታደሩ የጥላቻ ስሜት እንዲኖረው ሲያደርግ ነበር ያሉት ሜጀር ጄኔራል መርዳሳ፤ በዚህም ሠራዊቱን የማይመጥኑ ሃሳቦችን በመጠቀም በሕዝብ ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ሲጠቀም ቆይቷል ብለዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሀገርን ሰላምና አንድነት ለማስጠበቅ በሚያደርገው ጥረት ሠራዊቱን ከሕዝቡ ለመነጠል የስም ማጠልሸት ዘመቻውን እንደለመደው ቀጥሏል ያሉት ጄኔራሉ፤ ያም ሆኖ ግን ሕዝቡ ለሠራዊቱ ያለውን አድናቆት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እየገለጸ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአንጻሩ አሸባሪው ቡድን የሀገር መከላከያ ሠራዊት እያገኘ ያለውን የሕዝብ ድጋፍ እያገኘ ባለመሆኑና ወረራ በፈጸመባቸው አካባቢዎች ሁሉ እየተሸነፈ በመምጣቱ ቡድኑና ደጋፊዎቹ የሀገር መከላከያ ሠራዊትን ስም ለማጠልሸት የሀሰት መረጃና ፕሮፖጋንዳ እያሰራጩ እንደሚገኙም የቀድሞ ሠራዊት አባሉ ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ተናግረዋል።

የሀሰት መረጃና ፕሮፖጋንዳ ሕዝቡ በሠራዊቱ ላይ እምነት እንዲያጣ ብሎም እርስ በርሱ በጥርጣሬ እንዲተያይ ስለሚያደርግ ዜጎች ለሀሰተኛ መረጃዎች ጆሮ መስጠት የለባቸውም ያሉት ሜጀር ጀነራል መርዳሳ፤ በመንግሥት በኩል ተዓማኒነት ያላቸው መረጃዎችን በማቅረብ በሀሰት መረጃ የማይረበሽ ጠንካራ ሥነ-ልቦና ያለው ማሕበረሰብ መገንባትና ጉዳቱን መከላከል እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ለ27 ዓመታት ሀገሪቱን ሲበዘብዝና ሲያራቁት በነበረበት ወቅት ዋነኛ መሳሪያው ውሸት እንደነበር ጀነራሉ አስታውሰው፤ ዛሬ ላይ የሀሰት መረጃዎችን ቢያሰራጭና የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ቢያካሂድ አይገርምም ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት በጥፋት ተግባር የተሰማራው ሕወሓት አቅሙ እየተሟጠጠ በመሄዱ የሀሰት መረጃና ፕሮፖጋንዳን መርጨት አንድ የመንፈራገጫ ስልቱ አድርጎ እየተጠቀመበት ነው። ስለዚህ ሕዝቡ ተአማኒነት ካላቸው ምንጮች መረጃ በማግኘት ራሱን ከሕወሓት የሴራና የእርኩሰት እንቅስቃሴ ሊጠብቅ ይገባል ብለዋል፡፡

# "ሀገር እየተፈተነች...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የወርቅ ደረጃ እና 240 የብር ደረጃ ተሸላሚዎች ናቸው።

በሌላ በኩል በተከታታይ ለሦስት እና ከዚያ በላይ ዓመታት በፕላቲንየም ደረጃ ተሸላሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች ልዩ ተሸላሚ ሆነዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ቢ.ጂ.አይ ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ሄኒከን ቢራ ሼር ካምፓኒ እንዲሁም ሌሎች አሥር ተቋማት ለሦስት እና ከዚያ በላይ ተከታታይ ዓመታት በፕላቲኒየም ደረጃ ያሸነፉ ተቋማት ልዩ ተሸላሚ ሆነዋል።

በተጨማሪም አንድ ግለሰብ ግብር መሰወርና ማጭበርበርን በማጋለጥ ልዩ ተሸላሚ ሆነዋል። በ2014 በጀት ዓመት 360 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ የተሠራ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በድምሩ 336 ቢሊዮን 710 ሚሊዮን በላይ ብር ተሰብስቧል።

ከሀገር ውስጥ ታክስ 196 ቢሊዮን 211 ሚሊዮን በላይ ብር እንዲሁም ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ 140 ቢሊዮን 498 ሚሊዮን በላይ ብር ገቢ እንደተሰበሰበ የገቢዎች ሚኒስትሯ አብራርተዋል።

በ2014 በጀት ዓመት የላቀ አፈፃፀም ያላቸው የገቢዎች ሚኒስቴር ተሸላሚ ግብር ከፋዮች ምርጫ መስፈርቶችም የተገለፁ ሲሆን ግብር ከፋዩ አድራሻ እና ሌሎች መረጃዎች ማሟላት፤ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች ማስታወቅ እና የኦዲት ግኝት በግልና በታማኝነት ማስታወቅ እንዲሁም የግብርና ታክስ ስሌት ልዩነት ማሳወቅ የመሳሰሉ መስፈርቶች ከግምት ውስጥ መግባታቸው ተገልጿል፡፡

ገቢዎች ሚኒስቴር በ2011 በጀት ዓመት 198 ነጥብ 2 ቢሊዮን፣ በ2012 በጀት ዓመት 233 ነጥብ 7 ቢሊዮን ፣ በ2013 በጀት ዓመት 279 ነጥብ 4 ቢሊዮን እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት 336 ነጥብ 710 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡ የሚታወስ ነው።

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በቡራዩ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በቴክኖሎጂ ከበለጸጉ ሀገራት ተርታ እንዲያሰልፉ፣ እንደ ቡራዩ የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት ያሉ የተሰጥኦ ማዕከላትን ማብዛት ይገባል።

ኢትዮጵያ የምትቀየረው፤ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎችን የሚያበረታቱና የሚደግፉ ማዕከላት ሲስፋፉ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቡራዩ የተገነባው ልዩ የተሰጥኦ ትምህርት ቤት የተለየ የፈጠራ ሃሳብና ክህሎት ያላቸው ወጣቶችና ታዳጊዎች ለአገር ጥቅም ከፍተኛ ሚና እንዲያበረክቱ ያስችላል ብለዋል፡፡

አገር የሚቀየረው በወሬ ሳይሆን በፈጠራ መሆኑን ገልጸው፤ እነዚህ የልዩ ተሰጥኦ ባለቤቶችን የፈጠራ ሃሳባቸውን ወደ ተግባር የሚቀይሩበትና የሚያበለጽጉበት አውድ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ማድረግ ሲቻልም እነሱም ይጠቀማሉ፤ እኛም እንደ አገር እናተርፋለን ብለዋል፡፡

"ዓለማችን በቴክኖሎጂ መጥቃለች። ሀገራችን ኢትዮጵያም ቴክኖሎጂ ከሚያስገኛቸው እንደ ኢኮኖሚ ያሉ ትሩፋቶች ተጠቃሚ ለመሆን፣ በዘርፉ የላቀ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ማፍራቷ ግድ መሆኑን አመልክተው፤ ከየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚመጡ ወጣቶች ተሰጥኦቸውን የሚያጎለብቱበት ትምህርት ቤት ይሆናል ብለዋል፡፡

የትምህርት ቤቱ ግንባታ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ በልዩ ልዩ መንገድ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የአካባቢው ነዋሪዎችም ምስጋና አቅርበዋል፡፡

"የምንተባበር፤ የምንደማመጥ፤ በዘር በሃይማኖት የማንገፋፋ ስንሆን አገራችንን በቀላሉ ማሳደግ እንችላለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የሃሳብ ልዩነት ሳይገድበን አገራችንን በትብብር ማሳደግና ማበልጸግ ይኖርብናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ ያለው ነገር ይቆጫል፡፡ ትግራይ ሰላም ትሆናለች፣ ከትግራይ ወንድሞቻችን በጋራ የምናለማበት ጊዜ ቅርብ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መርቀው የከፈቱትና በቡራዩ ከተማ የተገነባው የልዩ ተሰጥኦ ትምህርት ቤት 708 ሚሊዮን 693 ሺህ ብር ወጪ ተደርጎበታል ። ይህ ትምህርት ቤት እስከ አንድ ሺህ ባለተሰጥኦዎችን ተቀብሎ የማስተናገድ አቅም እንዳለው ተጠቅሷል።

ፕሮጀክቱ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ በ 10 ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍ ሲሆን፤ ዛሬ የተመረቀው በአምስት ነጥብ አራት ሄክታር ላይ ያረፈው ፕሮጀክት ነው።

ትምህርት ቤቱ የባለተሰጥኦዎች ማደሪያ፣ የመመገቢያ አዳራሽ፣ የአስተዳደር ህንጻዎች፣ የህክምና ማዕከል፣ መማሪያ ክፍሎችና ቤተ ሙከራዎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡

የልዩ የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤቱ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አስፈላጊ ቁሳቁሶች የተሟላለት ሲሆን መጽሐፍ ፣ ኮምፒውተሮች፣ የቤተ ሙከራ ዕቃዎችንና ሌሎች አስፈላጊ ዕቃዎች የተሟሉለት መሆኑ ተጠቅሷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለትግራይ ሕዝብ ከኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በላይ ሊያስብለትና ሊጠነቀቅለት የሚችል ሌላ አካል የለም!

አሸባሪው ትህነግ ጦርነቶችን በመክፈት ለፈጠራቸው ችግሮች መፍትሄ ለማስቀመጥ የኢትዮጵያ መንግሥት ከጦርነት አማራጮች ይልቅ ሰላማዊ መንገድን በማስቀደም ብዙ ርቀት ተጉዟል፤ አሁንም እየተጓዘ ነው። ይህንንም በሕግ ማስከበር ዘመቻ ወቅት የተናጠል የተኩስ አቁም በማድረግ ከትግራይ ክልል ሠራዊቱን በማስወጣት፣ በጦርነቱ ወቅት በቁጥጥር ስር ውለው የነበሩ የቡድኑ አመራር አባላት ሳይቀር ክስ እንዲቋረጥ በማድረግና በመፍታት፣ የአፍሪካ ሕብረት የሰላም ንግግር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲካሄድ ዝግጁ በመሆን አረጋግጧል።

መንግሥት ምንጊዜም ቢሆን የትግራይን ሕዝብ የሚመለከተው ከአሻበሪው ቡድን ነጥሎ ነው። ይህንንም በሕግ ማስከበር ወቅት ለሕዝቡ በመጠንቀቅ እና ሰብአዊ አቅርቦቶችን እንዲያገኝ በማድረግ አረጋግጧል፤ ከሕግ ማስከበሩ ጎን ለጎን ሰብአዊ አቅርቦቶች ላይ በስፋት ሰርቷል፤ ቡድኑ ያወደማቸውን መሰረተ ልማቶች በአስቸኳይ በመጠገን መልሰው አገልግሎት እንዲሰጡ ብዙ ለፍቷል።

መንግሥት የተናጠል የተኩስ አቁም አድርጎ የትግራይ ክልልን ሲለቅ ለወራት የሚሆን የምግብ፣ የነዳጅና የመሳሰሉት አቅርቦቶች ለትግራይ ሕዝብ ትቶ ነው የወጣው። ወቅቱ የመኸር እርሻ የሚከናወንበት ስለነበርም በክልሉ ግብርና ቢሮ ከተጠየቀው በላይ የምርጥ ዘርና የማዳበሪያ ግብአቶችን ለክልሉ አርሶ አደር አቅርቧል። ከትግራይ ክልል ሠራዊቱን ሲያስወጣም ሕዝቡ ቆም ብሎ ራሱን እንዲመለከት እድል ሰጥቷል።

ይህ የመንግሥት ርብርብ ቡድኑ በአማራና በአፋር ክልሎች ላይ ያን ሁሉ ግፍ ሲፈጽምም ለአፍታም አልቆመም። ችግሩ ያለው ከትግራይ ሕዝብ ዘንድ ሳይሆን ቡድኑ ላይ እንደሆነ በማመን ለሕዝቡ የሚደረገው የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት በአየርም በምድርም ተጠናክሮ እንዲቀጥል አድርጓል።

ይህ እየሆነ ያለው ደግሞ ቡድኑ ለሕዝቡ የሚላከውን የሰብአዊ ድጋፍ፣ ነዳጅና የመሳሰሉትን እንዲሁም ድጋፎቹን ይዘው ወደ ክልሉ የሚሄዱ ከባድ ተሽከርካሪዎችን ለጦርነቱ ሊያውላቸው እንደሚችል እየታወቀም ነው። ዋጋ የተከፈለውና የሚከፈለው በአሸባሪው ቡድን የተነሳ የትግራይ ሕዝብ እንዳይጎዳ በማሰብ ነው።

ለትግራይ ሕዝብ ከማንም በላይ የሚያስቡት የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ናቸው እንጂ አሸባሪው ትህነግ አይደለም። መንግሥት የትግራይ ሕዝብ በአሸባሪው ቡድን መታገቱና ለሽብር ቡድኑ የጥፋት አጀንዳ መከለያ መደረጉ በእጅጉ ያሳስበዋል፤ ለዚህም ነው ሕዝቡ ከእዚህ እገታ እንዲላቀቅ ሲሰራ የቆየውና አሁንም እየሰራም ያለው።

የሽብር ቡድኑ የትግራይን ሕዝብ የሚፈልገው ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ለሚያካሂደው ሴራና ዘመቻ ሲል ብቻ ነው። ቡድኑ ሕዝቡን ከማምረት ስራው አፋትቶ፣ ትንሽ ትልቁ የልማት ሳይሆን የጦርነት ቋንቋ ብቻ እንዲናገር አርጎ፣ በቂ የእርዳታ አቅርቦት እያለም የትግራይ ሕዝብ ለረሃብ ሊጋለጥ ነው እያለ በማሚረት ለዓለም አቀፍ ተቋማት የሚጮኸው ለትግራይ ሕዝብ አስቦ አይደለም፤ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ለሚያካሂዳቸው ጦርነቶች ስንቅና ትጥቅ ለማሰባሰብ፣ ሌሎች የኢትዮጵያ ጠላቶችን ከጎኑ ለማሰለፍ እንጂ፤ ይህንንም የቡድኑ የ1970ዎቹ ታሪኮችም ሆኑ በባለፉት ሁለት ዓመታት የከፈታቸው ጦርነቶች ቁልጭ አርገው ያመለክታሉ።

ለትግራይ ሕዝብ ቢያስብ አርሶ አደሩ ስለሚያስፈልገው ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች እና ስለትግራይ ልጆች ትምህርት ነበር መጨነቅ የነበረበት።

ይሁንና መልካም ነገር ስለማይጥመው ሥልጣን በኃይል ስለመቆናጠጥ ነው የሚያስበው፤ ለእዚህ ደግሞ የትኛውንም ዘግናኝ እርምጃ ስለመውሰድ ያወጣል፤ ያወርዳል። ስለሚያደርጋቸው ሴራዎች፣ ግጭቶች፣ ጦርነቶች፣ በሀገሪቱ ላይ ዓለም አቀፍ ጫናዎች እንዲደረጉ ነው የሚያወጣ የሚያወርደው። ከአንዴም ሶስቴ በዚህች ሀገር ላይ ጦርነት ሲከፍት ያደረገው ይህንኑ ነው።

ቡድኑ በሚከተለው ሰብአዊ ማእበል የተሰኘ ያረጀ ያፈጀ የጦርነት ስልት የትግራይ ጨቅላዎች፣ አባቶች፣ እናቶች፣ አካል ጉዳተኞች የእሳት ራት እንዲሆኑ አድርጓል። ለትግራይ ሕዝብ የተላከን የሰብአዊ ድጋፍ ለጦርነት ማዋል ለትግራይ ሕዝብ ማሰብ አይደለም፤ ልጁን ለታጣቂነት ላላቀረበ ቤተሰብ ሰብአዊ እርዳታ እንዳያገኝ ማድረግ ለትግራይ ሕዝብ ማሰብ ሊሆንም አይችልም። በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ላይ ጦርነት መክፈትም ለትግራይ ሕዝብ ጠብ የሚያደርግለት ነገር አይኖርም።

ለትግራይ ሕዝብ ማሰብ የሚሆነው ሕዝቡን ከቡድኑ በደም የተጨማለቀ መዳፍ ማላቀቅ፣ ሰብአዊ ድጋፍና የመሳሰሉትን በአስቸኳይ እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ መንግሥት የትግራይን ሕዝብ ከዚህ ታሪክ ይቅር ከማይለው የሽብር ቡድን ለማላቀቅ እየሰራ የሚገኘው።

በአሁኑ ወቅትም በሕግ ማስከበር ወቅት እንደተደረገው ሁሉ ከአሸባሪው ሕወሓት ነጻ በወጡ የትግራይ አካባቢዎችም ሰብአዊ ድጋፎች ተጠናክረው ቀጥለዋል። ሰሞኑን መንግሥት የሰጠው መግለጫም ይህንኑ ያረጋግጣል። በቀጣይም መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመር እንደሚሰራም ጠቁሟል።

ይህም ለትግራይ ሕዝብ ከኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በላይ ሊያስብለት የሚችል ሌላ አካል አለመኖሩ ቁልጭ ብሎ የታየበት ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የትግራይ ህዝብ ለራሱና ለመጪው ትውልዶች ሲል ...

**በእምነት**

ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ሁሉም ሰላም ነበር ፤ ሰራተኛው በስራ ገበታው፣ ተማሪው በትምህርቱ፣ ነጋዴው በንግዱ፣ ገበሬው በእርሻው ሁሉም በተሰማራበት መስክ ውጤታማ ለመሆን ተፍ ተፍ ሲል ነበር። ሁሉም የእለት ጉርሱን ከማግኘት ባሻገርም ህልሜ፣ ግቤ ብሎ ያስቀመጠውን ዓላማ እውን ለማድረግ ይተጋ ነበር፤ ይህ እውነታ በተመሳሳይ በትግራይም ይስተዋል ነበር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን በህዝባዊ እምቢተኛነት ከስልጣን የወረደው አሸባሪው ትህነግ ወደ ስልጣን ይመልሰኛል የሚለውን የመጨረሻ የጥፋት ተግባራትን፣ እኩይ ሴራዎችን ይጎነጉን ነበር፤ አገርን ከፍ ወዳለ ሁከትና ብጥብጥ በመክተት ከዚህ ለማትረፍ ቀን ከሌሊት ያለ እረፍት ይሰራ ነበር።

የጥፋቱና የሴራውን መጨረሻ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም በሰሜን እዝ ላይ ጥቃት በመሰንዘር በአደባባይ አረጋግጧል። በዚህ ፍጹም ከሆነ ከሀዲነት የመነጨው የቡድኑ ጥቃት፤ አገር እንደ አገር ከፍ ያለ የልብ ስብራት ውስጥ ገብታለች፡፡

እራሱን በነፃ አውጪ ስም ላለፉት አምስት አስርት አመታት ሲጠራ የነበረው ይህ አሸባሪ ቡድን፤ አገርና ህዝብ በአዲስ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ፤ ከፍ ባለ ተስፋ ተነቃቅተው መንቀሳቀስ በጀመሩ ማግስት በአገር ላይ የከፈተው ጦርነት ከሁሉም በላይ የለውጡ ተስፈኛ ለነበረው የትግራይ ህዝብ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖበታል።

አሸባሪ ቡድን "አገር ለማፍረስ እስከ ሲኦል እንወርዳለን" በሚል የጥፋት ጥግ የጀመረው ጦርነት እነሆ ላለፉት ሁለት ዓመታት ያህል የትግራይን ወጣት ለእልቂት፤ የትግራይን ህዝብ ተነግሮ ለማልቅ ማህበራዊ ምስቅልቅል ዳርጎታል።

መቼም ቢሆን ከስህተቱ የማይማረውና ከራሱ በላይ ለማንም የማይጨነቀው አሸባሪው ትህነግ የኢትዮጵያ መንግስት ሆነ ዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ለትግራይ ህዝብ የሚላከውን የእርዳታ እህል ሳይቀር በመንጠቅ ለቡድኑ ተዋጊዎች ቀለብ በማድረግ የራሱን ህልውና ለማስቀጠል የሄደበትም ኢሰብዓዊ መንገድና መንገዱ የትግራይን ህዝብ ያስከፈለው ዋጋ የቡድኑን የጭካኔ ጥግ ያመላከተ ነው።

የትግራይን ህዝብ በተደራጀ ጠንካራ መዋቅር የቡድኑ አስተሳሰብ ባሪያ በማድረግ ህዝቡ ምንም አይነት አማራጭ የፖለቲካ አማራጭ እንዳይኖረው አድርጓል። በዚህም ህዝቡ ፈርቶና ተገዶ አብሮት ለመቆየት ተገዷል። በዚህ ቆይታ ያተረፈው ነገር ቢኖር ልጆቹን ማጣት፣ በርሃብ ቸነፈር መገረፍን ብቻ ነው። ይህንን ደግሞ ከማንም ከምንም በላይ ራሱ ህዝቡ የሚያውቀው የሚመሰክረው ሃቅ ነው።

ቡድኑ እድሜውን ለማራዘም ብዙ ድንጋዮችን ፈንቅሏል። መንግስት የሰጠውን የሰላም እድል ጨምሮ በርካታ እድሎችንም አምክኗል። ከዛ ሁሉ በላይ ደግሞ ለህዝብና ለአገር ሲባል መንግስት ዝቅ ብሎ የሰላም ጥሪ አቅርቦ የእንደራደር መንገድን ከፍቶና ቢለውም አሁንም በእብሪት ያበጠው ልቡ አልረታ ብሎት እምቢታን መርጦ አገርን ለተደጋጋሚ እልቂት ዳርጓል።

በእውነት ሕዝቤ በሚለው ህዝብ ላይ እንደ አሸባሪው ትህነግ ግፍ የፈጸመና እየፈፀመ ያለ አረመኔያዊ ቡድን በዓለም ላይ ታይቶ ስለመታወቁ እኔ በግሌ እርግጠኛ አይደለሁም። የቡድኑን ያህል የስልጣን ጥማት ያለበትና አልጠግብ ባይ አለ ብዬ ለማሰብም እቸገራለሁ።

በእነዚህ ሁለት ዓመታት ህዝቡ ሕወሓትን በቃህ እንዲለው የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል ሰፊ ስራዎችም ተሰርተዋል። ሕዝቡ ካለበት አጣብቂኝ እና ከተሰራበት የከፋ ፕሮፓጋንዳ አንጻር ውጤታማነቱ የተጠበቀውን ያህል አልነበረም። ዛሬ ግን ነገሮች እየተቀየሩ ነው። ቡድኑ ከራሱ ጥቅም አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ እንዳይደለ የመጣበት መንገድ ለትግራይ ህዝብ በግልጽ እያሳየው ነው።

የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ አሁን ላይ ማድረግ ያለበት የሚመከረው የሚፈልግ አይደለም። በአሸባሪው ሕወሓት ላለፉት አምስት አስርት የደረሰበትን ግፍና በደል አስተዋሽ አይፈልግም። አሁን የሚፈልገው በቡድኑ ያጣውን ሰላምና ልማት ነው። አሸባሪው ትህነግና የትግራይ ህዝብ አንድ እንዳልሆኑ በገሃድ ማሳየት ነው። የትግራይ ህዝብ ትልቅ ማንነት ያለው፤ አገሩ እዚህ ለመድረሷ ከማንም በላይ ትልቅ ድርሻ የሚወስድና በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደር መሆኑን ማስመስከር ነው።

የትግራይ ህዝብ ይህንን አሸባሪ ቡድን በቃህ ከላዬ ውረድ፣ የምሰጥህ ልጅም፣ ሃብትም መሬትም የለኝም፤ በሰላም ልኑርበት ከእህት ከወንድሞቼ አትነጥለኝ ማለት ያለበት ትክክለኛ ጊዜ አሁንና አሁን ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ አሁነኛ አገራዊ እውነታው አመቺ ነው።

አዎ! በተለይም የኢትዮጵያ መንግስት በተቆጣጠራቸው የክልሉ ከተሞች የሚኖሩ ህዝቦች ከዓመታት በኋላ ያገኙትን የነጻነት አየር በቀላሉ ከእጃቸው እንዲወጣ መፍቀድ የለባቸውም። ለዚህም ከመከላከያ ሰራዊቱ ጎን በመቆም እንደውም ሌሎች አጎራባቾቻቸው እነሱ ያዩትን የነጻነት ብርሃን ብልጭታ እንዲያዩ በሚችሉት ሁሉ መደገፍ እንዳለባቸው ይሰማኛል። በእርግጥ ይህንን አያደርጉም የሚል ግምት የለኝም።

መንግስትም እነዚህን የተጎዱ ህዝቦች ለማገዝ ለመደገፍ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል አለበት። ለትግራይ ወንድሞቻችን ከምንም በላይ አሁን ሰብዓዊ እርዳታው የሚያስፈልጋቸው ወቅት ነው፤ ይህ እንዲሆን የሚሹ ብዙ ለጋሽ አካላት ያሉ ቢሆንም የእኛ ትኩረት ሊሆን የሚገባው ግን ከልባቸው የትግራይን ህዝብ ለመርዳት ፍላጎት ካላቸው ጋር ብቻ መሆን አለበት።

በጠቅላላው የትግራይ ህዝብ ማመን ያለበት ነገር የተሻለው ሕይወትና መጻኢ ተስፋ ያለው ከአሸባሪው ትህነግ ውጭ ነው። ህዝቡ ለራሱና ለመጪው ትውልዶች ሲል ጀርባው ላይ የታዘለበትን የወንበዴ ቡድን ወዲያ ገፍትሮ ጥሎ ለአመታት ያጣውን ነጻነት ብሎም ሰላምና ልማት በራሱ መንገድ ሊያስመልስ ፤ዳግም ከእጁ እንዳይወጣ በጥንቃቄ ሊጠብቀው ይገባል። አበቃሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ከፈረሱ ጋሪው እስከ መቼ ?

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ፈረስና ጋሪ ለአሁናዊው የአገራችን ሁኔታ ጥሩ ማሳያ ሆነው አግኝቻቸዋለው።ፈረስና ጋሪ ታሪክ የሚኖራቸው ቅደም ተከተላቸውን ሲጠብቁ ነው።ፈረስ ከኋላ ሆኖ ጋሪው ከፊት ከቀደመ የአገሬ ህዝብ እንደሚለው ከፈረሱ ጋሪው ይሆንና ውጥንቅጡ ይወጣል።እኛም እንዲህ ነን..ማስቀደም ያለብንን ሳናስቀድም ለዘመናት ከህዝብ በቀደመ የፖለቲካ ፊተኝነት ውጥንቅጣችን ወጥቶ ከርመናል።ባለማወቅ ሳይሆን በቸልተኝነት ፊትና ኋላነትን ባልጠበቀ ቅደም ተከተል ተፋልሰን ኖረናል።

አሁን የሚጠበቅብን የቦታ ለውጥ ነው።የቦታ ለውጥ የአስተሳሰብ ለውጥ ነው።ያለ ምንም ተግባር ከፈረሱ የቀደመውን ጋሪ ወደ ቦታው መልሶ የሳትናቸውን ቅደም ተከተሎች ማስተካከል ይኖርብናል። እኚህ የተፋለሱ ቅደም ተከተሎች ደግሞ ቦታቸውን የሚይዙት በእርቅና በምክክር ነው።በእርቅና በምክክር ችግሮቻችንን ፈልገን እንድናገኝ አገራዊ ምክክር ያስፈለገበት ዋና አላማም ለዚህ ነው።አሁን ጊዜው ከጋሪው ፈረሱ ቀድሞ በአንድ ልብ ወደ ፊት የምንሄድበት እንጂ ከፈረሱ ጋሪው እየቀደመ ስህተቶቻችንን እየደጋገምን የምንደነቃቀፍበት አይደለም፡፡

አገር የልዕልና ጥግ ናት።ይህ የእኔና የእናንተ፣ ያንቺም የእሱም የሁላችንም እውነት ነው።አገር መከበሪያ ናት፣ በትላንት በዛሬና ነጋችን ውስጥ የተሳለች ምስል ናት። አገር የእያንዳንዳችን የማንነት ማህተማችን ናት።ስለ አገር ሲነሳ ጥላሁን ገሰሰ ትዝ ይለኛል።ስለ አገር ሲነሳ በባንዲራዋ ፊት ያነባው ኃይሌ ገብረ ስላሴ ይታወሰኛል። አገር ይቺ ናት..በልባችን በነፍሳችንም ውስጥ ያለች፣ የትም ይዘናት የምንዞር። ስሟን በሰማን ቁጥር፣ ባንዲራዋን ባየን ቁጥር እንባችን የሚመጣ፣ ስለ ደግ ህዝብ ሲወራ ባር ባር የሚለን ይቺ ናት አገር። ይቺን ነው ኢትዮጵያ የምላችሁ፡፡

ስለ አገራቸው ክብር ደማቸውን ያፈሰሱ፣ አጥንታቸውን የከሰከሱ፣ ከአገሬ በፊት እኔን ያሉ በርካታ ኢትዮጵያዊያን እዛም እዚም ሞልተዋል።እነ በላይ ዘለቀ፣ እነ አብዲሳ አጋ፣ እነ ዘርዐይ ደረስ የአገር ፍቅርን ጥግ ድረስ ያሳዩን ምልክቶቻችን ናቸው።እነሱ በዘመን ውስጥ ሳይደበዝዙ ያበሩት ቅደም ተከተላቸውን ሳይስቱ ፈረስና ጋሪ ሆነው ነው። እኛም ሳንደበዝዝ እንድናበራ የእይታ መነጽራችንን ማስተካከል ይኖርብናል። ከዘነጋነው ወይም ደግሞ አውቀን ከሰወርነው የዝባዝንኬ ጨዋታ ወጥተን አገርና ህዝብን በሚጠቅም እውነት በሆነ ስፍራ ላይ መቆም ይጠበቅብናል፡፡

አገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እስኪጠፋን ድረስ መጉደል የለብንም።ሩጫው ሁሉ ወደአልተፈለገ አቅጣጫ ከማድረግ ወጥተን መስተካከል አለብን። ከእውቀት ማነስና ከኃላፊነት መጉደል አሁን ላይ ጭራሽ የምናየው፣ የምንሰማው ሁሉ ከኢትዮጵያዊነት ባህልና ስርዐት ያፈነገጠ የጭካኔ የመጨረሻው ማሳያ እየሆነ የመጣበት ጊዜ ላይ ነን።ወጣቱ በምክንያት ከመኖር ይልቅ በስሜት መመራትን የመረጠበት ጊዜ፣ የተማረው በእውቀቱ አገር ከመጥቀም ይልቅ የውሸት ተረት እየፈጠረ በህዝቦች መካከል የጠብ ቁርሾ መንዛትን የተካነበት ዘመን ላይ ነን።

በየቦታው በየአገሩ የምንሰማው አንድ አይነት ሆኗል።ሀዘን፣ ሞት፣ ስደት ያልሰማንበት ጊዜ የለም።በየቀኑ በየሚዲያው የምንሰማው ክፉ ወሬ ብቻ ነው።በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ ይሄ ሁሉ በደልና ጭቆና እየደረሰ ያለው ተማርን በሚሉ ራስ ወዳዶች መሆኑ ነው። ከአገርና ህዝብ ሀብት ላይ ቀለብ እየተሰፈረላቸው ተምረው መፍትሄ እንደመሆን ተመልሰው አገር የሚያፈርሱ ተበራክተዋል። ያጎረሳቸውን የእናታቸውን እጅ የሚነክሱ ወጪት ሰባሪ ትውልድ የበዛበት አስከፊ ዘመን ላይ ደርሰናል። የእስካሁኗ ኢትዮጵያ ባልተማሩ ልጆቿ የተሰራች ናት። የእስካሁኗ ኢትዮጵያ የፍቅርና የአንድነት የደም ፍሬ ናት። ይሄ ሁሉ ገናናነታችን በነሱ የመጣ ነው።ለዚች አገር እኛ የዋልነው ውለታ የለም።እኛ የተሰራ ከማፍረስ፣ አንድ ሆኖ የቆመን ህዝብ ከመለያየት ባለፈ አሁን ላለችው ኢትዮጵያ ምንም አይነት ጥቅም እየሰጠን አይደለም፡፡

እኛ የአገር ጠባቂ እንጂ ጠላት አይደለንም።የአገራችንን ህመም ስናስብ ህመሟ ሁሉ በእኛ የመጣ እንደሆነ እንደርስበታለን።ዛሬም እያሳመምናት ያለነው እኛ ልጆቿ ነን።አገራችን በሌሎች ታማ አታውቅም።ህመሞቿ እኛ ነን።እኛው እንዳንገላት አፈራለው።ይሄ እንዳይሆን ከፈረሱ ጋሪው የሆነ ፖለቲካና ፖለቲካዊ አስተሳሰባችን መጽዳትና መስተካከል አለበት።በብዙ ችግር፣ በብዙ ድህነት፣ በብዙ ማጣትም ተተብትባ የምትኖር አገር ተስፋዋን በሰነቀችብን በእኛ መጎሳቆሏ እንደ አንድ ወጣት ሳስበው ያመኛል።ወጣቱ ከጦርነት ወጥቶ ለልማት የሚታጠቅበት፣ አዛውንቶች ከስደት ወጥተው ለእርቅ የሚቀመጡባት ኢትዮጵያ ናፍቃኛለች።ህጻናት ከርሀብ ወጥተው ለነገ ተስፋ የሚሆኑባት፣ የተማሩት ከነውጥ ወጥተው ለወገን አለኝታ የሚሆኑባት ጦቢያ ናፍቃኛለች።

ከፈረሱ ጋሪው በሆነ የራስ ወዳድነት ልክፍት ወጣቱን ለልማት ከመጠቀም ይልቅ ጦርና መሳሪያ አስታጥቀው ለእኩይ አላማ የሚያሰለጥኑ፣ መብቱን በሰለጠነ መንገድ ከመጠየቅ ይልቅ በረብሻ እንዲጠይቅ በማድረግ የግል ጥቅማቸውን ለማስፈጸም የሚለፉ ባንዳዎች እየተፈጠሩ ነው።አሁን ላይ በየቦታው በሰው ህይወትና በንብረት ላይ የሚደርሱ ውድመቶች ሁሉ ስሜታዊውን ወጣት መጠቀሚያ በማድረግ የተከሰቱ ናቸው።እነሱ በሞቀ ቤታቸው ጮማ እየቆረጡ፣ ውስኪ እየተጎነጩ ተቀምጠው ወጣቱን በጊዜአዊ ጥቅም በመደለል ወደ እሳት የሚማግዱ እኩዮች አሉ፡፡

> **አሁን ላይ በየቦታው በሰው ህይወትና በንብረት ላይ የሚደርሱ ውድመቶች ሁሉ ስሜታዊውን ወጣት መጠቀሚያ በማድረግ የተከሰቱ ናቸው። እነሱ በሞቀ ቤታቸው ጨማ እየቆረጡ፣ ውስኪ እየተጎነጩ ተቀምጠው ወጣቱን በጊዜአዊ ጥቅም በመደለል ወደ እሳት የሚማግዱ እኩዮች አሉ**

ቆይ መማራችን ለአገርና ወገን ካልሆነ ጥቅሙ ምን ላይ ነው? እኔ ካልተጠቀምኩ፣ የእኛ ሀሳብ ካልሆነ በሚል አጉል አስተሳሰብ የነገውን ተስፈኛ ወጣት ለጥፋት ማነሳሳት ተገቢ ነው ብዬ አላስብም። በአገራችን ውስጧ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎችን ገንብታ እያስተማረች የተማረ የታጣባት አገር ሆነናል።አለም በስልጣኔ መጥቃ ጨረቃ ላይ ቤቷን በሰራችበት በዚህ ስልጡን ዘመን ላይ እየኖርን ለአለም ስልጣኔ ፈር ቀዳጅ የሆነን ቀደምት ህዝቦች እኛ እርስ በርስ መግባባት አለመቻላችን የምንጊዜም ጥያቄዬ ሆኖ ጭንቅላቴ ውስጥ አለ።

እስኪ እንግባባ።አንተ ትብስ አንተ የሚለውን የጥንቱን ባህል ዛሬ ላይ መልሰን ከፈረሱ ጋሪው የሆነች አገራችን እንታደግበት። ኢትዮጵያዊነት ስርዐት እኮ ነው። ሀበሻነት ራሮት እኮ ነው።ፈርሰን መሰራት አለብን። ራስ ወዳድነት የወለደው ፖለቲካችን ህዝብን ከፊት አስቀድሞ እንደ አዲስ ነፍስ መዝራት አለበት። ወጣቱ በቤተሰቡ መሰራት አለበት።ፈርሀ እግዚአብሄር እንዲኖረው ሆኖ ማደግ አለበት።የተባረከ ሆኖ ስለ አገር ፍቅር እየተነገረው ማደግ ነገ ለሚኖረው ህይወት ወሳኝነት አለው፡፡

አሁን ላይ ነውጥ የሚፈጥሩ፣ ለአገር ስጋት ሆነው የምናያቸው ሰዎች በስርዐት ያላደጉ የነውረኛ ቤተሰብ ልጆች ናቸው። ሀገር..ሀገር ሆና እንድትቀጥል ታላላቆቹን የሚያከብር፣ የአባቶቹን ስርዐት ያልናቀ ትውልድ ያስፈልጋል። ከሰሞኑ ለሆን ጉዳይ ወደ አንድ ቦታ እየሄድኩ ታክሲ ውስጥ ተቀምጫለው። ታክሲ ቆሞላቸው አንድ አዛውንት እናት መንገድ ላይ ይሳፈራሉ።ከፊት ለፊት ቦታ ስላልነበረ ኋላ ወንበር መቀመጥ ግድ ነበረባቸውና በዛ እርጅና ኋላ ወንበር ላይ መጉላላቱን ስላልፈለጉት ከፊት የተቀመጠውን ወጣት ‹የኔ ልጅ ቦታ አትቀይረኝም..› አሉት፡፡

ወጣቱም ‹ኋላ መቀመጥ አልወድም› ሲል መለሰላቸው፡ ይሄ መልስ ታክሲ ውስጥ የተሳፈርነውን ሁላችንንም ያሳዘነ መልስ ነበር። በሚቀጥለው ወንበር ላይ የተቀመጡ አንድ አባት በወጣቱ ንግግር እያዘኑ ‹ምናለበት ብትነሳላት? መታዘዝክ እኮ ትልቅነትክን ነው የሚያሳየው› ሲሉት፡፡

‹እኔን ከሚሉ ለምን እርሶ አይነሱም? ሲል ትዕቢታዊ ምላሽ ሰጣቸው።መልስ አልሰጡትም..በልባቸው ግን ትውልዱን የሚረግሙ ይመስለኛል።‹አምላኬ ሆይ ምነው እዚህ ዘመን ላይ ጣልከኝ? የሚሉ።ለባልቴቷ ቦታቸውን ለቀው ኋላ ወንበር ተቀምጠው ሲተክዙ ነበር፡፡

ብዙ የአለም አገሮች ልጆቻቸውን የሚያስጠኑት አንድ አባባል አለ..‹አገሬ ለኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለአገሬ ምን አደረኩላት› የሚል።ይህ አባባል የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረው የጆን ኦፍ ኬኔዲ ይሁን እንጂ ብዙ አገራት የሚጋሩት እውነት ነው።ብዙ ኢትዮጵያዊያን ከአገር መውሰድ እንጂ ለአገር መስጠትን አያውቁበትም። የሁልጊዜ ጥያቄያቸው አገሬ ለኔ ምን አደረገችልኝ የሚል ነው። እንዲህ አይነት እኩይ አመለካከት አገር ከመጉዳት ባለፈ ጥቅም የለውም፡፡

ይሄ አስተሳሰብ ነው ዛሬ ላይ አገር እየጎዳ ያለው። ለሙስናና ስልጣንን ያላግባብ ለሚጠቀሙ ህገ ወጦች በር የከፈተው።ወጣቱ ለአገሩ ተስፋና የብልጽግና ምንጭ እንጂ የጥፋት ምክንያት መሆን የለበትም።በመልካም ሀሳብ ተሞልቶ ለወገኑ አለኝታ እንጂ ስጋት የመሆኑ ነገር ማክተም አለበት።አባቶቻችን ታላቅ አገርና ታላቅ ህዝብ እንዳስረከቡን ሁሉ እኛም ለነገ ልጆቻችን የምናስረክባት መልካምና በሁሉ ነገሯ የምትደነቅ አገር ልንፈጥር ይገባናል።ይሄ የመንግስት ወይም የተወሰኑ ሰዎች ኃላፊነት ሳይሆን የሁላችንም ኃላፊነት ነው፡፡

መማር ማለት መፍትሄ መሆን ማለት ነው።እኛ ግን እውቀታችንን ጥበባችንን ሁሉ አገር ለማፍረስና ለዘመናት ተዋዶና ተከባብሮ ተቻችሎም የሚኖርን ህዝብ ለመከፋፈል እየተጠቀምንበት እንገኛለን። ከአገርና ከህዝብ ጥቅም ይልቅ ራስ ተኮር ሆነን ብዙ የሆነችልንን አገርና ህዝብ ስንጎዳ ስናስጎዳም ቆይተናል። መማራችን ምኑ ላይ እንደሆነ አልገባኝም። የድሮ አባቶቻችን ባልሰለጠነ ዘመን አክሱምና ላሊበላን የመሰለ ለዘመናዊው አለም ትንግርት የሆነ ታላቅ የስልጣኔ ምልክትን ትተውልን ከማለፋቸውም ባሻገር በአንድነቷ የምትደነቅን አገር ሰርተውልን አልፈዋል።

እኛ ተማርን የምንለውና እጅግ በሰለጠነው ዘመን ላይ ያለነው የዛሬዎቹ ግን ያልተማሩ አባቶቻችን ያወረሱንን ታላቅ አገር በማፍረስ ደፋ ቀና እንላለን። በህዝቦች መካከል ጥላቻና መለያየት እንዲኖር፣ በፍቅር ፈንታ ጥላቻን፣ በአንድነት ፈንታ መለያየትን በመስበክ ለአገራችንም ለህዝባችንም ነቀርሳ ሆነን እየኖርን ነው። የአገራችን መከራ ፈደል በቆጠሩና ከስማቸው በፊት ማዕረግ በቀጠሉ ግለሰቦችና ቡድኖች የተፈበረከ ነው፡፡

እስኪ ምን ያህሉ የተማረ ዜጋ ነው ለዚች አገር መድህን ሲሆን ያያችሁት? ጎኗ ላይ ተጣብቀው እንደ መዥገር ደሟን ከመምጠጥ ባለፈ የፈየዱት መላ አለ ብዬ አላስብም። አስተምራ ለቁም ነገር አብቅታቸው ነበር፣ ካላት ላይ ከሌላት ላይም ቀንሳ ቀን አውጥታቸው ነበር፣ በድህነት ጎኗ ብዙ ብዙ ሆናላቸው ነበር ዛሬ ላይ ለክብሯ ፊታውራሪ ከመሆን ይልቅ ውርደቷን ናፍቀው ከፊት ቆመው በለው ይላሉ።

ድህነት ለዘመናት ተብትቦ በያዛት አገር ላይ እንዲህ አይነት ጭካኔ ስርየት የሌለው በደል ሆኖ ነው የሚታየኝ። በፖለቲካው በኢኮኖሚው በማህበራዊው በሁሉም ውስጥ የከፋት እጃቸው አለ። በእውቀታቸው ውስጥ እውነት የለም።በልባቸው ውስጥ አምላክ የለም። ትላንት ራስ ወዳድ ነበሩ ዛሬም ራስ ወዳድ ሆነው ይኖራሉ። ይበቃናል..አሁን ደግሞ ቀና እንበል። ከፈረሱ ጋሪው ቀድሞ ሲያሰቃየን ከነበረው የፖለቲካ አስተሳሰብ እንውጣ።በእርቅና በምክክር የፈረሱን ቦታ ለጋሪው፣ የጋሪውን ለፈረሱ ሰጥተን ልክ በሆነ ቅደም ተከተል አገር እንስራ፡፡

የእርቅና የመቻቻል ባህል ያስፈልገናል።የአንድነት የፍቅር አለም መገንባት ግድ ይለናል።ተምረን የተገነባ ከማፍረስ፣ መኪና ከማቃጠል፣ ህዝብ ከማፈናቀል የዘለለ ለዚች ድሀ አገር ውለታ መዋል አለብን። አሁን ላይ ህዝብ የጦርነት ወሬ መስማት ሰልችቶታል።አሁን ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ሰላም፣ እንደ አንድነት የናፈቀው ምንም የለም።እስኪ ለአፍታ እናስብ..ከፈረሱ ጋሪው በሆነ የፖለቲካ ስርዐት ተራምደን ግራ የተጋባች አገር ፈጥረናል፡፡

እስኪ አሁን ደግሞ በፍቅርና በእርቅ ከጋሪው ፈረሱ የሚቀድምባትን ኢትዮጵያ እንፍጠር።ፈረሱ እኮ ህዝብ ነው..ጋሪው ደግሞ ፖለቲካ።እስከዛሬ ፖለቲካው ቀድሞ ህዝብ እየተከተለ ከማንወጣው ማጥ ውስጥ ገብተናል። እስኪ ደግሞ ህዝብ ይቅደምና ፖለቲካ ይከተል።ከጥያቄ በቀር መልስ በሌላት አገር ላይ ነን።በቀን ሶስቴ መብላት ባቃተው ድሀ ህዝብ መካከል፤ በስራ ማጣት መሄጃ ባጣ ወጣት መካከል ነን፣ የውስጥና የውጪ አገራዊ አጀንዳ የበረከተበት ሰሞን ላይ ነን።ለመፍትሄ እናምጥ እንጂ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አንሁን።

# የአገር በቀል እውቀት ዓለም አቀፋዊና አሁናዊ ይዞታ

ግርማ መንግሥቴ

በዛሬው እትማችን እንነጋገርበት ዘንድ አቅደን የመጣነው ስለ "አገር በቀል እውቀት" ምንነትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ስላለው ወቅታዊ ሁኔታና ይዞታ ነውና አቻ ትርጉሙ Indigenous Knowledge የሚለው፤ በተለዋዋጭነትም Traditional Knowledge መሆኑን ከወዲሁ መግለፅ ተገቢ ይሆናል።

ብያኔውን በተመለከተ ከዚህ በፊት በተያያዥ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ሀሳብ በተለዋወጥንበት ወቅት "አገር በቀል እውቀት ማለት ..." ካልን በኋላ፤

አገር በቀል እውቀት ማለት በውስን አካባቢዎች ላይ በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ዙሪያ ላሉ ክፍተቶች መፍትሄ ይሆኑ ዘንድ ባህላዊ በሆነ መንገድ በአንድ ወይም በተወሰኑ ሰዎች የሚመነጭና የሚተገበር እውቀት ነው፡፡ በእንግሊዘኛው በዋናነት "Indigenous knowledge" የሚለው የሚገልፀው ሲሆን "Traditional knowledge" ወይም "Local knowledge" የሚሉትም ሊተኩት ይችላሉ፡፡

የማህበረሰብ እውቀት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ የህይወት ገፅታዎች የሚዳሰሱበትና መፍትሄ የሚሰጥበት የተገለፀና ያልተገለፀ እውቀትና ልምድን ያጠቃለለ ነው፡፡ በብዙ ዘመናት ልምድ የዳበረና በባህል ውስጥ ሰርፆ ከትውልድ ትውልድ በታሪክ፣ በዘፈን፣ በአባባል፣ በእምነት እና በሌሎች መንገዶች በአካባቢው ቋንቋ የሚተላለፍ እውቀት ነው፡፡ እውቀቶቹ በተገኙበት ቦታ ምንጭ ለሆኑት ግለሰብና ቤተሰብ የተሰጠ ልዩ ጥበብ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በአብዛኛው ግን በጊዜ ሂደት በአካባቢው ማህበረሰብ እየተለመደና እየሰፋ ሲመጣ የማህበረሰቡ የጋራ ንብረት ይሆናል፡፡

እንደ አገራችን ባሉ በተፈጥሮ ሀብት በበለፀጉ አገራት በተለይ በግብርና፣ በጤና እና በአካባቢ ጥበቃ ዘርፎች የአገር በቀል እውቀቶች እና ቴክኖሎጂዎች ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም በትራንስፖርት ዘርፉ የአገር በቀል እውቀቶች እና ቴክኖሎጂዎች ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ በግብርናው ዘርፍ የእፅዋትና አዝርእት ተከላ፣ መረጣና አሰባሰብ ሂደት፣ በእንስሳት እርባታና አያያዝ ስርዓት እና ለመሳሰሉት ተግባራት መሠረት የሚሆን በግለሰብና በማህበረሰብ ውስጥ የዳበሩ ብዙ እውቀቶች አሉ፡፡ በማለት አገራዊ ምንጮችን (ከወደ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ያገኘነውን መረጃ) ጠቅሰን ማስቀመጣችን ይታወሳል።

እርግጥ ነው ከአንዳንድ የሙያና ጥናት ዘርፎች ህክምናና ቋንቋ ጥናት (medicine እና linguistics) አካባቢ ካልሆነ በስተቀር አገር በቀል እውቀት ይሁነኝ ተብሎ በትምህርት ተቋማት ውስጥ አይሰጥም። በእነዚህ የጥናት መስኮች ግን ለአገር ባህል እውቀቶች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራባቸዋል። ይህን ስንል ግን ሁሉም ጋ ማለታችን አይደለም፤ የነቁት ጋ እንጂ።

ባጭሩ አገር በቀል እውቀት (በነገራችን ላይ፣ እኛ አገር በቀል እውቀት እያልን እንነጋገር እንጂ በባለሙያዎች እይታ Indigenous knowledge, Traditional Indigenous knowledge; Indigenous Knowledge Systems and Practices (IKSPs) በሚል ተለያይተው የሚጠኑ ዘርፎች መኖራቸውን ማስታወስ ተገቢ ይሆናል። ይህንን ስንል ግን የሚጋሯቸው ጉዳዮች ወይም ብያኔዎች የሉም ማለታችን አይደለም።)

ይህንን ስያሜ፣ ገነነ ብዙነህ "ሀገረሰብ ትምህርት በኢትዮጵያ" በምትልና ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ ... አይነት ፈገግታን የምታሳየው ስራቸው ውስጥ "አገርፈለቅ እውቀት" (2006 ዓ.ም) ማለታቸውን አክለን፤ ለዛሬውም ይኸው ብያኔ ይሰራልና በዚሁ አልፈነው ወደ ፋይዳና ይዞታው እንሂድ። ከአፍሪካም እንጀምር።

ኤፕሪል 2022 ለአደባባይ የበቃውና African Indigenous Knowledge Systems and the World የሚል ርእስ የተሰጠው ጥናት እንደሚያመለክተው፤ አፍሪካ የሚያዋጣት የራሷን አህጉር በቀል እውቀቶች ይዛ ወደ ስራ መግባት እንጂ ሌላ አይደለም።

ናይጄሪያዊው ስመ ጥር ደራሲ ቺና አቼቤ በዝነኛ ስራው (Things Fall Apart, 1958) አጉልቶ ያሳየው ይህንኑ የናይጄሪን አገር በቀል እውቀቶች ሲሆን፣ ጊዜውን በተመለከተም በተለይ ቅድመ ቅኝ አገዛዝ የነበረውን በማሳየት ድህረ ቅኝ (በ19ኛው ክፍለ ዘመን) አገዛዝ የደረሰውም ውድመት ያመላከተ ስራ ነው።

ይህ መጽሐፍ በአቢይነት የሚያንፀባርቀው በቅድመ የአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ የናይጄሪያው ቱባው አገር በቀል እውቀት ምን መልክ እንደነበረው፤ ማንነትን፣ ባህልን ... ከመግለፅና ማንፀባረቅ አኳያ የነበረውን ጉልህ ሚና ሲሆን፤ በአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ ዘመን ያንን ቱባ አገር በቀል እውቀት ከስሩ በመንቀል ናይጄሪያውያንን ከማንነታቸው የመነጠል ክፉ ስራ እየተሰራ እንደ ነበር፤ ይህ ደግሞ በፍፁም መሆንና መቀጠል እንደሌለበት አስረግጦ የሚሄድ ሆኖ፤ ይህም በኢቦ ማህበረሰብ (Igbo society)ና ከሱ በወጣው፣ በዋናው ገፀ ባህርይ Okonkwo አማካኝነት በሚገባ የተንፀባረቀ ሆኖ ታይቷል።

ይህ በልቦለድ መልክ የቀረበ፣ በአቀራረቡ ቀላል የሆነ፣ በናይጄሪያ የኢቦን ማህበረሰብ ባህልና አገር በቀል እውቀት ፍንትው አድርጎ ያሳየ .... መጽሐፍ ወደ እውነቱ ወይም ታሪካዊነቱ ያዘነበለ (allegorical or perhaps closer to historical fiction) ሆኖ እንጂ የተገኘው እንደማንኛውም ልቦለድ በፈጠራነቱ ብቻ የተፈረጀ ሆኖ አልታለፈም። በተለይ በቅድመ ቅኝ አገዛዝ ዘመን ሳይበረዝና ሳይከለስ የኖረው ቱባው የናይጄሪያውያን ባህል በቅኝ አገዛዝ ዘመን ምን ያህል እንደተደፈረ፣ እንደተበረዘና እንደ ተከለሰ፤ ይህም (በዋናው ገፀባህርይ Okonkwo አማካይነት ለማሳያት እንደ ተሞከረው) ምን ያህል ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የማንነት ቀውስን ሁሉ እንዳስከተለ ከእግር ጥፍር እስከ ራስ ጠጉር እያብጠረጠረ ያሳየ መፅሀፍ ነው።

ይህንን እዚህ ማንሳት ምናልባትም በወካይነት ሁሉንም የአፍሪካን አገር በቀል እውቀቶችንና ቱባውን አፍሪካዊ ባህል ያሳያል በሚል ሲሆን፤ አገር በቀል እውቀትን በተመለከተ በአፍሪካ ደረጃ ተመሳሳይ ግንዛቤ እየተያዘ ይገኛል።

ይህ ተመሳሳይ ግንዛቤ በአፍሪካ ደረጃ መኖሩ በማንኛውም መልኩ ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ ምናልባት አስቀድመው ቅኝ ገዥ በነበሩት አሁንም ያ ለምን ይቆማል የሚል አስተሳሰብ ባላቸው ወገኖች ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል። ይህም የጥቅም ጉዳይ ነውና ቢኖር የማይገርም ሲሆን ዋናው ነገር ችግሩን በመሰረታዊነት ለመፍታት የአፍሪካውያን አንድነት አስፈላጊ የመሆኑ ጉዳይ አጠያያቂ መሆን የለበትም።

በቅርቡ የአፍሪካ ህብረት (ኤዩ) ባወጣው መግለጫ ላይ እንዳመለከተው የአፍሪካ አገር በቀል እውቀቶች ከዚህ መለስ የሚባሉ እንዳልሆኑ፤ በቀኝ አገዛዝ ኃይሎች እንዲጠፉ የመደረግን ሙከራ ሁሉ ተቋቁመው እዚህ የደረሱ መሆናቸውን፤ እነዚህ ቱባ አፍሪካዊ እሴቶች ለአፍሪካውያን የማንነት መገለጫዎች መሆናቸውን፤ እነዚህን ወደ ልማትና እድገት መሳሪያነት መጠቀም እንደሚገባ ... ወዘተ አብራርቶ አስፍሯል። (ለዝርዝሩ የድርጅቱን ድረ-ገጽ መመልከት ይቻላል።)

በአንዳንድ ልሂቃን ነን በሚሉ ሰዎች የኋላ ቀርነት መገለጫ ተደርጎ ሲወሰድ የነበረውን የአገር በቀል እውቀት (IK) መሰረታዊ ፋይዳ በተመለከተ በርካታ ጥናቶች ያሉ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት እየወጡ ያሉት፣ ሁሉም በሚባል ደረጃ እያመለከቱ የሚገኙት አገር በቀል እውቀት በተለይ ለአርሶ አደሩ ማህበረሰብ ስለ ተለያዩ ተግባራትና እንቅስቃሴዎች ውሳኔ ከመስጠት ጀምሮ በግብርናውና ትምህርቱ ዘርፍ ለህይወታቸው ተስማሚና የሚበጅ በሆነ መልኩ ስራ ላይ ያውሉት ዘንድ የሚያደርግ እውቀት ነው።

ይህ መደበኛ ያልሆነ የእውቀት ምንጭ በተለይ አገር በቀል እውቁቱ ባለበት አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች የሚሰጠው ጥቅም የዋዛ አይደለም። (በጥናቶች "provides problem-solving strategies for local communities" እንደተባለው ማለት ነው።)

የአገር በቀል እውቀት ሚና የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ጀምሮ የሰዎችንና እንስሳትን ጤንነት ለመጠበቅ፣ ከተፈጥሮ ጋር ያለን ትስስር ለማወቅና ለማጥበቅ፣ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም፣ እና ሌሎች በርካታ ወሳኝ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን፤ ብሎም ለመቆጣጠር ማስቻል ድረስ የዘለቀ ነው።

"እነዚህን አገር በቀል እውቀቶች እንዴት አድርጎ ከማጥፋት፣ ከመከለስና መበረዝ ... መጠበቅ ይቻላል?" የሚል ጥያቄ ብዙውን ጊዜ ሲነሳ የሚሰማ ሲሆን፣ ለዚህ መልስ ይሆን ዘንድ የፊሊፒንስ መልካም ተሞክሮ መሰረት በማድረግ መልስ የሚሰጡ ሲሆን፤ እሱም የባለቤትነት መብትን በማስከበር፣ ምልክቶችን በማድረግ፣ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥን አመላካች ምልክቶችን መጠቀም፤ እውቅና መስጠት ... የሚል ነው።

ሌላውና አገር በቀል እውቀቶችን እንዴት አድርጎ ከጥፋትና መጥፋት መታደግ ይቻላል ለሚለው የሚሰጠው መልስ ትልቁ የአገር በቀል እውቀት ጠላት ዝመና (Modernization) ሲሆን፣ ይህንን መከላከል እንኳን የማይቻል ቢሆንም የጥፋት እጁን ነባሩን ባህልና እሴት ማውደም ላይ እንዳያሳርፍ አስፈላጊው ጥንቃቄ ሁሉ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው።

ይህ መዘመንና ነባር ማንነትን የመንቀል ተግባር በአንድ አገር ወይም አህጉር ላይ የተወሰነ ሳይሆን አጠቃላይ ዓለምን ያጥለቀለቀ ችግር እንደ መሆኑ መጠን ለመፍትሄውም አጠቃላይ የዓለምን ንቅናቄና የመፍትሄ ርምጃ የሚፈልግ ይሆናል።

ዛሬ በመላው ዓለም በከፍተኛ ደረጃ እውቅናን ያገኘውና በየአውዱ ተዘውታሪነት ያለው አገር በቀል እውቀት በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ይዞታ በእጅጉ የተለያየ ነው። ለምሳሌ በአፍሪካና ኤዥያ አካባቢ፣ ማለትም አልበለፀጉም የሚባሉት ስፍራዎች ያሉት አገር በቀል እውቀቶች ጭራሽም ያልተነኩና ልማትም ላይ ያልዋሉ (underutilized resources) ሲሆን፤ በአንፃሩ ደግሞ በምእራቡ አለምና አሜሪካ አካባቢ ቀድሞውንም የዳበረ ባህላዊ እሴቶች የሌላቸው መሆኑን ተከትሎ እዚህ ግባ የሚባል አገር በቀል እውቀት የለም።

ይህ አገር በቀል እውቀት ባለመኖሩም ምክንያት ወደ ፈጠራውና ሰው ሰራሽ ምርቶች (ሸቀጦች) በቀጥታ መግባት ጀመሩ። ይህ እየተስፋፋ ሄደ። በመሆኑም ያላደጉ አገራትን መንፈሳዊና ባህላዊ እሴቶች ኋላ ቀር (outdated) በማለት ለማፈራረስ ደፋ ቀና ማለትን ተያያዙት። የተሳካላቸው የመኖሩን ያህል ግን በአብዛኛው አልተሳካላቸውም።

ይሁን እንጂ "ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ" የሚለውን ጨምሮ፣ በበርካታ የአለማችን አገራት የአገር በቀል እውቀት እጅጉን ተፈላጊ እየሆነ መጥቷል። በተለይ ከተፈጥሮ አምርሮ እየተጣላ የሚገኘው የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር መልሶ ለመታረቅ፣ የአየር ንብረት ለውጥና የመሳሰሉትን ችግሮች ለመፍታት ... መፍትሄው አገር በቀል እውቀቶችን ማወቅ፣ ማልማት፣ መጠበቅና በስራ ላይም ማዋል መተኪያ የሌለው መሆኑን እየተገነዘበ ያለ ይመስላል።

**የትና መቼ**

በተለያዩ መንገዶች እንደተረጋገጠው፣ አገር በቀል እውቀት የማይገባበት፣ የማያስፈልግበት ጊዜና ቦታ፤ ሙያና ዘርፍ ... የለም። ለምሳሌ ያህል እንኳን በትምህርቱ ዘርፍ (ከላይ የህክምናውንና ሥነቋንቋን ጉዳይ በተመለከተ ያነሳነው እንዳለ ሆኖ) ያለውን ወስደን መመልከት እንችላለን።

ሁሌም፣ አገራችንን ጨምሮ (ለምሳሌ ያህል፣ በፈረንጆቹ በ1972 የወጣውን የትምህርት ሴክተር ሪቪው፣ በ1994 የወጣውን የኢትዮጵያ የትምህርት ስትራቴጂ ይመለከታል)፣ አገር በቀል እውቀት በትምህርቱ መስክ አስፈላጊነቱ አሻሚ ሆኖ አያውቅም። ችግሩ ስርአተ ትምህርቱ ውስጥ ማካተትና ወደ ተግባር ማሸጋገር አለመቻሉ ላይ ነው። ሁሉም፣ በተለይ ዘመናዊ ትምህርት ወደ አገራችን ገባ ከተባለ ወዲህ አገር በቀል እውቀትን እንደ ኋላ ቀር ቆጥሮ (በፈረንጆቹ "ጠቃሚ" ምክር ምክንያት) ከስርአተ ትምህርቱ ውስጥ እስከ ማስወገድ ተዘለቀ። ይህም፣ ከትውልዶች የስነ ምግባር ጉድለት ጀምሮ ከፍተኛ ጉዳትን ማስከተሉ እየታየ ሲሆን፤ አሁንም መፍትሄው ፊትን ወደ አገር በቀል እውቀት ማዞርና እሱኑ በመፍትሄነት መጠቀም እንጂ ሌላ እንዳልሆነ ነው እየተመከረ ያለው።

በቅርቡ፣ ጃንዋሪ 2022 ለንባብ የበቃ አንድ ዓለም አቀፍ የምርምር ውጤትም አገር በቀል እውቀት በትምህርቱ ዘርፍ የሚያስገኛቸውን መሰረታዊ ፋይዳዎች የዘረዘረ ሲሆን፤ በተማሪዎች መካከል አብሮነትን፣ ትብብርን፣ ልምድ ልውውጥን፣ አብሮ ማደግና መስራትን ... ወዘተ ያሰርፃል። ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ተማሪዎችን ቁጥር ይቀንሳል። የአካባቢያቸውን ባህል ይገነዘባሉ። ይህ በበኩሉ ወደ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲያቀኑም ያደርጋል።

አንድ ህብረተሰብ፣ ለረዥም ጊዜያት ከተፈጥሮ ጋር በነበረው ተራክብኦ መነሻነት ያዳበረው ግንዛቤ፣ ክህሎት፣ ፍልስፍና ... መሆኑን በመረዳት ለአገር በቀል እውቀት(ቶች) "the understandings, skills and philosophies developed by societies with long histories of interaction with their natural surroundings." የሚል ብያኔን ያስቀመጠው ዩኔስኮ፣ አለማችን አሁን ለተጋረጠባት ችግር፣ ማለትም ኮቪድ-19፣ የአየር ንብረት ለውጥ ... እና የመሳሰሉት ሁሉ መፍትሄው አገር በቀል እውቀትን ተግባራዊ ማድረግ ነው። (እንደ አንዳንድ ምሁራን ጥናት ኮቪድን ተከትሎ በአደጉት አገራት አማካኝነት ለአፍሪካ የታዘዙትና ተግባራዊ የተደረጉት (በሁሉም ባይሆን) ርምጃዎች (ለምሳሌ ፍፁም ከቤት አለመውጣት) የአፍሪካ አገር በቀል እውቀትን ያገናዘቡ ሳይሆኑ የፈረንጆቹን አፍሪካን ዳግም የማደህየት ስትራቴጂም መሰረት ያደረጉ ናቸው። ሌሎችም ብዙ አሉ።)

ባጠቃላይ፣ በአሁኑ ሰዓት ዓለም ፊቱን ወደ አገር በቀል እውቀት የመለሰበት ጊዜ ላይ ነው የምንገኘው። የጥናትና መርምር ስራዎችና አጥኚዎቻቸውም ብእራቸውን ወደዚሁ ካደረጉ ቆዩ። በመሆኑም፣ በተለይም አፍሪካን የመሳሰሉና በአገር በቀል እውቀት የበለፀጉት አህጉራት ፊታቸውን ወደዚሁ ቱባና እምቅ ሀብታቸው በማዞር፣ የአፍሪካ ህብረት "አጀንዳ 2063ን ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው አገር በቀል እውቀትን ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው" እንዳለው ሁሉ፣ በአገራት ደረጃም (ከግለሰብ ጀምሮ) ይህንኑ ሊከተሉና እጃቸው ላይ ባለው ሀብት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል።

> ይሁን እንጂ "ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ" የሚለውን ጨምሮ፣ በበርካታ የአለማችን አገራት የአገር በቀል እውቀት እጅጉን ተፈላጊ እየሆነ መጥቷል። በተለይ ከተፈጥሮ አምርሮ እየተጣላ የሚገኘው የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር መልሶ ለመታረቅ፣ የአየር ንብረት ለውጥና የመሳሰሉትን ችግሮች ለመፍታት ... መፍትሄው አገር በቀል እውቀቶችን ማወቅ፣ ማልማት፣ መጠበቅና በስራ ላይም ማዋል መተኪያ የሌለው መሆኑን እየተገነዘበ ያለ ይመስላል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# የወጣቶችን ተጠቃሚነት በ‹‹ከፍታ››

**አስናቀ ፀጋዬ**

ወጣት ይድነቃቸው ተረፈ ትውልድና እድገቱ በደብረብርሃን ከተማ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪውን በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ከደብረብርሃን ዩኒቨር ሲቲ አግኝቷል። ሁለተኛውን ዲግሪውን ደግሞ በማኔጅመንት ተቀብሏል። በተማረባቸው የትምህርት መስኮች በተለያዩ የግልና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ተቀጥሮ አገልግሏል።

በግሉ የማቀዝቀዣና የድራፍት ማሽኖች ጥገና ስራም ሰርቷል።በቀበሌ አካባቢ በሚካሄዱ የወጣቶች እንቅስቃሴዎች ውስጥም ንቁ ተሳታፊ ነበር።የማነቃቂያ ፕሮግራሞችንም ሰርቷል።በስነተዋልዶ ጤናና በፀረ ኤች አይቪ ኤድስ ክበቦች ውስጥም በንቃት ተሳትፏል።



ወጣት ይድነቃቸው ተረፈ፤



አቶ ኤርሚያስ አሰፋ፤

‹‹ከፍታ›› ስለተሰኘው ፕሮጀክት መረጃው ቢኖረውም ጉዳዩን ቀለል አድርጎ ሲመለከተው እንደነበር የሚናገረው ወጣት ይድነቃቸው ስለከፍታ ምንነት በተመለከተ እርሱን ጨምሮ ለሌሎች የደብረብርሃን ወጣቶች ገለፃ ሲደረግ ስለፕሮጀክቱ ምንነት በጥልቀት እንደተረዳ ይገልፃል። በተለይ ደግሞ ታለንት ዩዝ አሶሴሽን ወጣቱ ማህረሰብ ከድንጋይ ወርዋሪነት ወደ ድንጋይ ደርዳሪነት እናምጣው፤ ድንጋይ ለመወርወር ምክንያት የሆነውን እንቅረፍለት የሚለው ሃሳብ ይበልጡን እንደሳበውና ወደዚህ ፕሮጀክት ለመግባት እንደገፋፋው ያስረዳል። በአሁኑ ግዜ ደግሞ የደብረብረሃን ከፍታ ወጣቶች ህብረት ጥምረትና የገንዘብ ብድርና ቁጠባ ተቋም ሊቀመንበር መሆኑን ይገልፃል።

እንደ ወጣት ይድነቃቸው ማብራሪያ የከፍታ ፕሮጀክት እንደ ደብረብርሃን ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ተመስርቷል።ሲመሰረትም ከክፍለ ከተማ ጀምሮ ከተለያዩ ክበቦች የተውጣጡ፣ ማህበረሰቡን የሚወክሉና አካል ጉዳተኛ ወጣቶች የተካተቱበት በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል።ከ103 የወጣት ክበቦች ውስጥ የተውጣጣ 11 ውህደት በመፍጠር ፕሮጀክቱ ተጀምሯል።

‹‹ከፍታ›› ፕሮጀክቱ ይፋ እንደሆነ ስለምንነቱና ስለሚሰራባቸው ስራዎች እንዲብራራ ተደርጓል። በመቀጠልም በውህደት ጥምረት ማህበሩ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ከፍታን በተመለከተ የያዙትን እውቀት ለሌሎች ወጣቶች አሳውቀዋል። ይህንንም ለማሳካት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴዎች ተዳርገዋል።ወጣቱ የከፍታ ፅንሰ ሃሳብን ከተረዳ በኋላ ወደ 24 ያህል የሚሆኑ የተለያዩ ስልጠናዎችን እንዲያገኝ ተደርጓል።

በኋላ ላይ ደግሞ በከፍታ ፕሮጀክት ውስጥ አዲስ ፅንሰ ሀሳብ መጣና የገንዘብ ብድርና ቁጠባ ተጀመረ። ይህ የገንዘብ ተቋም ለወጣቱ የገንዘብ ቁጠባና ብድር በማመቻቸቱ ለወጣቱ ተጨማሪ የስራ እድል ፈጥሯል። በተለይ ደግሞ ወጣቱ የተለያዩ የቢዝነስ ሃሳቦች ቢኖሩትም የመስሪያ ገንዘብ ስለማይኖረው ወደ ተግባር ለመግባት ይቸገር ነበር። በከተማዋ ውስጥ ሌሎች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ተቋማት ቢኖሩ እንኳን ገንዘብ ለመበደር ማስያዣ ስለሚጠይቁ አብዛኞቹ ወጣቶች ገንዘቡን ማግኘት አይችሉም።ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ የከፍታ ፕሮጀክት በዚሁ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ተቋም አንድ ወጣት ከሌላኛው ጋር እንዲጣመርና ዋስ እንዲሆን በማድረግ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ አክሲዎን መሸጥ ተጀመረ።

የአንድ አክሲዎን ዋጋ 250 ብር እንዲሆንና ወጣቱ ዝቅተኛውን አራት የአክሲዎን ዋጋ እንዲገዛ ተደረገ።ወራሃዊ ቁጠባ 300 እንዲሆንም ተወሰነ። በዚህም ለበርካታ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች 50 ሺ ብር የሚሆን አክሲዎን ተሸጠ።በአሁኑ ግዜ ደግሞ ከ150 ሺ በላይ አክሲዎን ተሸጧል።ይህ ጠቃሚ መሆኑን ተረዱ ወጣቶችም የገንዘብ ተቋምን መቀላቀል ጀመሩ። በቅርቡ ደግሞ ቢሮ በመከራይቱ ተቋሙ ሙሉ ስራውን ይጀምራል።

ወጣት ይድነቃቸውም ከሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ፕሮጀክቱን መቀላቀሉን ተናግሮ፤ በዚህ ፕሮጀክት ታቅፈው የሚሰሩ ወጣቶች 4 ሺ መድ ረሳቸውን ይጠቁማል። የገንዘብ ብድርና ቁጠባ አገልግሎቱን በተመለከተ ደግሞ ከ200 ሺ በላይ የሚሆኑ ወጣቶች አክሲዎን በመግዛት ላይ እንደሚገኙ ያመለክታል። ወጣቶቹ አክሲዎን ከገዙ በኋላ በትንሹ 300 ብር በወር እየቆጠቡ መስራት ለሚፈልጓቸው ማንኛውም የቢዝነስ አይነቶች አራት እጥፍ ብድር የሚያገኙ ይሆናል።

በአሁኑ ግዜ ልክ እንደሌሎቹ ወጣቶቹ ሁሉ እርሱም በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ በመታቀፍና የራሱን ሀሳብ በማመንጨት ወደ ቢዝነስ ለመግባት ሃሳብ እንዳለውም ጠቁሞ በተለይ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ተቋሙ ሙሉ በሙሉ ስራውን ሲጀምር ሃሳቡን ወደ ተግባር ለመለወጥ ትልቅ እድል እንደሚፈጥርለት ተማምኗል። አክሲዎን በመግዛቱ ደግሞ ሀሳቡን ከጫፍ ለማድረስ አንድ እርምጃ አንዳንደረደረው ይገልፃል።

ልክ እንደ እርሱ ሁሉ ሌሎችም ወጣቶች በእንዲህ አይነቱ ፕሮጀክት ውስጥ ገብተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በቅድሚያ ራሳቸውን ሊለውጡ የሚችሉ አጋጣሚዎችን መጠቀም እንደሚኖርባቸው ይመክራል።የንቁ ዜጋ መገለጫውም ይኸው ነው ይላል።

ታለንት ዩዝ አሶሴሽን በተሰኘው አገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ የፕሮግራም ማናጀር አቶ ኤርሚያስ አሰፋ እንደሚናገሩት ድርጅቱ በዋናነት ወጣቶች ላይ አተኩሮ የሚሰራ ሲሆን ከተቋቋመ ሀያ አመታትን አስቆጥሯል። በነዚህ አመታት ውስጥ በተለይ በወጣቶች የስነ ተዋልዶ ጤናና በሌሎች አጠቃላይ የጤና ጉዳዮች ተደራሽነትና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት አገልግሎቶች ላይ ሰፋፊ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ወጣቶችን ወካይ የሆኑ ስርአቶችን በመዘርጋትም እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በዚህም እድሜያቸው ከ15 እስከ 29 የሚሆኑ በርካታ ወጣቶችን በተለያዩ ፕሮጀክቶች ድጋፍ እንዲያገኙ አድርጓል። አዲስ አበባን ጨምሮ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አማራና አፋር ክልሎች ላይ ወጣት ተኮር ስራዎችን አከናውኗል።

በአሁኑ ግዜ ደግሞ ድርጅቱ ‹‹ከፍታ›› የተሰኘ ለአምስት አመት የሚቆይ ትልቅ ፕሮጀክት ጀምሯል። ፕሮጀክቱም በዩ ኤ ስ ኤድ የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወን ሲሆን አዲስ አበባ እና ደብረብረሃን ላይ 460 ሺ ወጣቶችን ተደራሽ በማድረግ እየተተገበረ ይገኛል። ፕሮጀክቱ ተግባራዊ መሆን ከጀመረም ሁለት አመት አስቆጥሯል።

በዚሁ ፕሮጀክት ለወጣቶች ተደራሽ የሚሆኑ የጤና አገልግሎቶችን በኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ በወጣት ማዕከላት፣ በጤና ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች እየተሰጡ ይገኛሉ። ለወጣቶች ተደራሽነት ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት አገልግሎቶችም በብድርና ቁጠባና በአቅም ግንባታና የህይወት ክህሎት ስልጠናዎች በነዚሁ ማእከላት እንዲቀርቡ እየተደረገ ነው።

**ስ**አብነትም በስፖርት፣ በስነ ጥበብ፣ በቴክኖሎጂና በሌሎችም ጉዳዮች እንዲደራጁ በመለየት፣ በመመዝገብና በማሰልጠን የወጣት ማህበራት ጥምረት በማቋቋም እርስበርስ የሚረዳዱበት፣ ሀሳብ የሚለዋወጡበት፣ በወጣቶች ጉዳዮች ላይ ድምፃቸውን የሚያሰሙበትና በአገራቸው ጉዳይ ላይ የሚወያዩበት መድረክ ተፈጥሯል።

ፕሮጀክቱ ወጣቶች በተቀናጀ መልኩ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ የሚያስችል ሲሆን ሁለት መሰረታዊ ግቦችን ይዟል። የመጀመሪያው ግብ ወጣቶች ዲሞክራሲያዊ በሆነና እነሱን በሚወክል መድረክ ውስጥ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ነው። ለዚህም ወጣቶቹ በተለያዩ ፍላጎቶቻው ለአብነትም በስፖርት፣ በስነ ጥበብ፣ በቴክኖሎጂና በሌሎችም ጉዳዮች እንዲደራጁ በመለየት፣ በመመዝገብና በማሰልጠን የወጣት ማህበራት ጥምረት በማቋቋም እርስበርስ የሚረዳዱበት፣ ሀሳብ የሚለዋወጡበት፣ በወጣቶች ጉዳዮች ላይ ድምፃቸውን የሚያሰሙበትና በአገራቸው ጉዳይ ላይ የሚወያዩበት መድረክ ተፈጥሯል።

በዚሁ መሰረት በደብረብርሃን ከተማ አንድ የወጣቶች ጥምረት ተቋሟል። በአዲስ አበባም በሰባት ክፍለ ከተሞች ማለትም በየካ፣ ለሚ ኩራ፣ ጉለሌ፣ አዲስ ከተማ፣ አራዳ፣ ልደታና ቂርቆስ ክፍለከተሞች ላይ ሁለት የወጣት ጥምረቶች ተቋቁመዋል።

ሁለተኛው ግብ ፈጠራ የታከለበትና ወጣት መር የፈንድ ማግኛ መንገዶችን መፍጠር ሲሆን ይህም በወጣቶች የሚመራ ሲሆን ወጣቶች በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ስልጠናዎችና የብድርና ቁጠባ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችል ነው።

እንደ አቶ ኤርሚያስ ማብራሪያ እነዚህን ሁለት መሰረታዊ ግቦች ዕውን ለማድረግ ደግሞ ሶስት ደጋፊ ግቦች አሉ። አንደኛው /youth capacity for advocacy and agency/ ሲሆን በወጣቶች ጉዳይ፣ ጤና፣ ትምህርት፣ ኢኮኖሚና ውክልና ላይ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ አቅማቸውን ማጎልበት፣ ራሳቸውን በማውጣት ለማህበረሰቡና ለመንግስት እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል። በዚህ ላይ የአደቮኬሲ፣ አጀንዳ ሴቲንግ፣ ሲቪክ ኢንጌጅመንት ስልጠናዎች ወጣቶቹ እንዲያገኙ ይደረጋል።

ይህም ወጣቶች በማህረሰባቸው ውስጥ ያሉ ችግሮችን ነቅሰው አውጥተው ለማህበረሰባቸው መልሰው ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።የተቸገሩ አዛውንቶችን እንዲያግዙ፣ ያረጁ ቤቶቻውን እንዲያድሱ፣ የተጎዱ ትምህርት ቤቶችን እንዲደግፉ፤ እንዲጠግኑና በመሰል ስራዎች ወጣቶች ከችግር ፈጣሪነት ወደ መፍትሄ አካልነት እንዲሸጋገሩ የሚያደርግ ነው።

ሁለተኛው አዳዲስ የኢኮኖሚ እድሎችን በተለይ ተቀጥረው መስራት ለማይፈልጉ ወጣቶች ስራ መፍጠር ሲሆን እነዚህን ወጣቶች በመለየት የቢዝነስ ክህሎት፣ የኢንተርፕሪነርሺፕ፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎቶችን እንዴት ማግኘትና መጠቀም እንደሚችሉ፣ የህይወት ክህሎት፣ የሲቪክ ተሳትፎና ሌሎችም ስልጠናዎች እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

በመቀጠል ደግሞ ወጣቶች ብድርና ቁጠባ እንዲያገኙ በዚሁ ፕሮጀክት በተቋቋመው ‹‹ዩዝ ኢምፓ ወርመንት ፈንድ›› በቡድንም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል። ዚህም በደብረ ብርሃን ከተማ አንድ ትልቅ የወጣቶች የብድርና ቁጠባ ህብረት ስራ ማህበር ተቋቁማል። በሀአሁኑ ግዜም ማህበሩ ተደራጅቶ ሼር እየሸጠ ይገኛል።

አባላት ከዚህ ፈንድ ከሚያገኙት ብቻ ሳይሆን ራሳቸው በሚቆጥቡት ገንዘብ ለትምህርት፣ ለቢዝነስና ለተለያዩ ለሚፈልጓቸው አገልግሎቶች ብድር መበደር ይችላሉ።ተቀጥረው መስራት ለሚፈልጉ ወጣቶች ደግሞ በተቀጠሩበት የስራ መስክ ውጤታማ እንዲሆኑ፣ ስራ መፈለግና ሲቪ ማዘጋጀት እንዲችሉ ስልጠናዎች ይሰጣቸዋል።

የስራ እድል እንዲመቻችላቸውም ይደረጋል። ለአብነትም ለዳሸን ባንክ ከ300 በላይ የሚሆኑ ወጣቶችን ማስቀጠር ተችሏል።የኢንተርፕረነርሺፕ አገልግሎቶችም ለወጣቶቹ እንዲመቻች ይደረጋል። በፍቃደኝነት ስራ እንዲለማመዱ የሚደረግበት ሁኔታም ይመቻቻል። የስራ ፍለጋ ክህሎታቸውን በማዳበር ስራ ራሳቸው ፈልገው የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲኖርም ስልጠናዎች ይሰጣቸዋል። ለዚህም ድርጅቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከተግባረ ዕድ ኮሌጅና ደረጃ ዶት ኮም ከተሰኘ የኦንላይን ፕላትፎርም ጋር አብሮ ይሰራል።በቅርቡ 53 ቀጣሪ ኩባንያዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች የተሳተፉበት ቀጣሪ ከተቀጣሪ የተገናኙበት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል።

ሶስተኛው እነዚህን አገልግሎቶች ለወጣቶቹ ተደራሽ ለማድረግ ድርጅቱ የለያቸው የወጣት ማእከላት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የጤና ተቋማት፣ የብድርና ቁጠባ ተቋማትንና የማህበራዊ ሚዲያውን ይጠቀማል።በተጨማሪም የወጣት ማእከላትና የጤና ተቋማትን በመረከብ ለወጣቶቹ ምቹና ሳቢ እንዲሆኑ ይታደሳሉ።ለወጣት ሴቶችና ለአካል ጉዳተኞችም ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገው ይሰራሉ።ለዚህም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ከተግባረ እድ ኮሌጅ ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ወደ ስራ ሊገባ ነው።

አቶ ኤርሚያስ እንደሚሉት አዲስ አበባ ተግባረ እድ ኮሌጅ ውስጥ ለሚገኙ ከ7 ሺ በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች የተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥቷቸዋል።ሰልጣኞችንም ወደነዚህ ጥምረቶች በማምጣት የቁጠባና ብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስራዎች ይሰራሉ።

በሚነድፉት ፕሮጀክቶች ውስጥ በትንሹ 50 ከመቶ ያህሉ ሴቶች እንዲሆኑ ተደርጎ እየተሰራ ነው። ከዚህ ፕሮጀክት 6 ከመቶ ተጠቃሚነት ደግሞ ለአካል ጉዳተኞች ተሰጥቷል።

‹‹ከፍታ›› ፕሮጀክት በ17 የአገሪቱ ከተሞች ተግባራዊ እየሆነ የሚገኝ ሲሆን ታለንት ዩዝ አሶሴሽን ደግሞ አገልግሎቱን በአዲስ አበባና ደብረ ብረሃን ከተማ ይሰጣል፤ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆንም በሌሎች አካባዎች ላይ ይሰራል።

# የምድር በረከት

# ስብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ግብአት አቅርቦት - የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሄዎች

**ስምስም መንግሥቱ**

ትላልቅ አገራዊ ፕሮጀክቶችን፣ የመኖሪያ ቤቶችን፣ እንደ መንገድ እና ድልድይ እንዲሁም የጤናና የትምህርት፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የመስኖ መሰረተ ልማቶች፣ ወዘተ. ያሉትን ለመገንባት ሲታሰብ ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብአቶች መካከል ብረት ይጠቀሳል።ሰፊ የልማት እቅድ ያለው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ከእድገታቸውና ከልማታቸው ጋር የሚጣጣም የብረት ግብአት አቅርቦት ሊኖራቸው ይገባል።

በዚህ ወቅት በመሠረተ ልማት፣ በቤቶች ልማትና በመሳሰሉት ዘርፎች ሰፋፊ ስራዎችን እያካሄደች ላለችው ኢትዮጵያ ደግሞ የብረት አቅርቦት እጅግ ወሳኝ ነው። በዚህ ወቅት ምክንያታዊና ምክንያታዊ ባልሆነ ግብይት ሳቢያ ጣራ እየነካ ባለው የብረት ዋጋ እነዚህን መሰረተ ልማቶችና የተለያዩ ግንባታዎችን ለማካሄድ ብረት ከውጭ በግዥ በማስገባት የልማት ሥራውን ማስቀጠል የሚታሰብ አይደለም።የዋጋ ንረቱ የግንባታውን ኢንዱስትሪ ፈተና ውስጥ ጥሎታል።ችግሩ የቅሬታ ምንጭ መሆን ከጀመረም አመታት ተቆጥረዋል፡፡

ከማዕድን ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ኢትዮጵያ በ2013 እና 2014 በጀት አመት ብቻ ለብረትና ብረት ነክ ውጤቶች ግዥ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊየን ዶላር ወጪ አድርጋለች። አገሪቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየገጠማት ባለው የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እጥረት፣ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ላለፉት ሁለት አመታት የዘለቀው ጦርነትና እሱን ተከትሎ በአገሪቱ ላይ የተደረጉ ጫናዎች፣ በተለያዩ ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየጨመረ የመጣው ዋጋ የውጭ ምንዛሬ በመመደብ በግዥ የብረት ግብአትን ለመሠረተ ልማት ለማቅረብ ታደርግ የነበረውን ጥረት በእጅጉ እየተፈታተኑት ይገኛሉ፡፡


መንግስት ይህን ችግር በመፍታት የመሠረተ ልማትና ሌሎች ግንባታዎችን ለማስቀጠል የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወሰድ ቆይቷል፤ አሁንም የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን ነድፎ መፍትሄዎችን እያመቻቸ ነው።

በመሰረቱ የዘርፉን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ምድር ውስጥ ካሉ የተፈጥሮ ፀጋዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የብረት ማዕድን ወይንም ጥሬ ሀብት በጥናትና ምርምር ለይቶና አደራጅቶ በዘርፉ ላይ ልምድ ያላቸው ኩባንያዎች እንዲያለሙ በማድረግ የግብአት አቅርቦቱን ችግር መፍታት ይጠበቃል፡፡

ኢትዮጵያ ለልማቷና ለዕድገቷ ሊያግዛት የሚችል የብረት ማእድን ሃብት ባለቤት ስለመሆኗ ይገለጻል።መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በብረት ዘመን የሮማን ኢምፓየር ያመርት የነበረው የብረት መጠን 85000 ቶን ሲሆን፣ ቻይና ደግሞ በአመት 5000 ቶን ብረት ታመርት ነበር። በኢትዮጵያ በጥናት የተረጋገጠ 300,145,000 ቶን የብረት ማዕድን አላት።ከዚህ ውስጥ 72,508,575 ቶን የተረጋገጠ ክምችት ኩባንያዎች እንዲያለሙት የምርት ፈቃድ ተሰጥቷል።የተቀሩት በጥራትና መጠናቸው ላይ ተጨማሪ ጥናት የሚፈልጉ ናቸው፡፡

የተለያዩ ኩባንያዎች በአማራ፣ በትግራይና በኦሮሚያ የፍለጋና የምርት ፈቃድ ወስደው በስራ ላይ ይገኛሉ።ከእነዚህም መካከል ሰቆጣ ማይኒንግ፣ ኤም ኤስ ፒ ስቲልና ኮዬጻ ማይኒን ሼር ኩባንያ (Koyetsa Mining share company) ይጠቀሳል።

መረጃው እንዳመለከተው፤ በጥናት የተረጋገጠው የብረት ማእድን ክምችት ጥቅም ላይ ቢውል ለብዙ አመታት እፎይታን የሚያስገኝ ነው።እነዚህን የቆዩ መረጃዎች መነሻ ወይንም መሠረት በማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራው ቢጠናከር በግብአት አቅርቦት ራስን ለመቻል ተስፋ የሚሰጥ ነገር ስለመኖሩ መረዳት



ከምድር ውስጥ የሚገኘው የማዕድን ሀብት፤



ለአምራች ኢንዱስትሪው የሚውለው የብረት ግብአት፤

ይቻላል።አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታም ለዘርፉ የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ያስገድዳል። የማእድን ሚኒስቴር ከሰሞኑ ይፋ ያደረጋቸው መረጃዎች ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት የሚያሳዩ ናቸው።ለዘርፉ ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሄ ብሎ አስቀምጧል።

የመንግሥትና የህዝብ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ የፈሰሰበት አገር ውስጥ ያለውን የብረት ሀብት በአግባቡ ፈትሾ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ሲገባ ሀብቱ እየባከነ መሆኑን የማእድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ዑማ አስታውቀዋል። ያገለገለውን ብረት መልሶ ጥቅም ላይ ባለመዋሉ የአካባቢ ብክለት እያስከተለ አገርን እየጎዳ መሆኑን በመጥቀስም ሚኒስትሩ በዘርፉ የሚስተዋለውን ሌላውን ክፍተትም አሳይተዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ይህን ተደራራቢ ጉዳት ለማስቀረት የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።ከአገልግሎት ውጭ የሆነው የባቡር ሐዲድ እንዲሁም አገልግሎታቸውን የጨረሱ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች፣ ቁርጥራጭ ብረቶች እርሳቸው የሚመሩትን ተቋምና ተጠሪ መሥሪያ ቤቶችን ጨምሮ በቀድሞ ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ)፣ በመከላከያ፣ በኢትዮ ቴሌኮም፣ በአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች ልማት አስተዳደር በአጠቃላይ በእያንዳንዱ የልማት ድርጅት ውስጥ ብቻ በሚሊዮን ቶን የሚቆጠር የብረት ክምችት ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በፌዴራል መንግሥት ተቋማት፣ ተጠሪ ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኮሌጆች፣ በሁሉም ከተማ አስተዳደሮች፣ ክልሎችና በግለሰቦች ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት ተከማችቷል። ይህ በየአካባቢው የሚገኘው አገልግሎቱን የጨረሰና ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ግብአት ሊሆን የሚችል የብረት ክምችት ቢያንስ ለሚቀጥሉት ሁለት አመታት የብረት ግብአት ለሚፈልጉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሊውል የሚችልም ነው፡፡

የዘርፉን የግብአት አቅርቦት ችግር በጊዜያዊነት በዚህ መልኩ ከመፍታት በተጨማሪ ለግዥ የሚወጣውን ወደ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊየን ዶላር ማዳን ወይም ማትረፍ ይቻላል ያሉት ሚኒስትሩ፣ ለብረት ግዥ ይወጣ የነበረውን ገንዘብም እንደ ማዳበሪያ ላሉ አገራዊ ጥቅም ላላቸው ግዥዎች ማዋል የሚቻልበትን ዕድል መፍጠር እንደሚቻልም ይጠቁማሉ፡፡

ለዚህ ጊዜያዊ ችግር መፍቻ ተብሎ በመንግሥት የተቀመጠውን የመፍትሄ አቅጣጫ አስመልክቶ ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ እንዳስረዱት፤ የብረት ሀብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ብክነትን ለማስቀረት መንግሥት አዲስ የፖሊሲና የማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ ወደ ትግበራ ገብቷል።በዚሁ መሠረትም ባለቤት ያላቸውንም ሆነ የሌላቸውን ያገለገሉ ብረታ ብረቶችን ለብረታ ብረት ፋብሪካዎች በቀጥታ ሽያጭ እንዲተላለፉ ለማድረግ በመንግሥት ተወስኗል።

የብረታ ብረት ቁርጥራጮች ሽያጩም ገንዘብ ሚኒስቴር ባዘጋጀው የመነሻ ዋጋ እና ማዕድን ሚኒስቴር በመደበው የፋብሪካዎች የማምረት አቅም መሠረት ይከናወናል። የማስፈጸሙ ሥራውም በግብረ ኃይል የሚመራ ሲሆን፣ ይህም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት፣ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በማዕድን ሚኒስቴር እንዲሁም በክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች በተዋረድ በጋራ ይከናወናል። በፌዴራል መንግስት፣ በክልሎች፣ በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ያሉት የመንግሥት መዋቅሮችም የማስፈጸም ግዴታና ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ያገለገሉ የተሽከርካሪ፣ ማሽነሪና መሰል የብረታ ብረት ክምችቶችን ይዞ መገኘት ተጠያቂነትን ያስከትላል። በትግበራ ላይ የሚገኘው ይህ የማሻሻያ እርምጃ አፈጻጸም በየወሩ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በሪፖርት የሚቀርብ ይሆናል። ይህን አገራዊ ተልእኮ ያለውን እንቅስቃሴ መደገፍ ከሁሉም ይጠበቃል፡፡

እንዲህ ባለው ጊዜያዊ መፍትሄ የአምራች ኢንዱስትሪው የግብአት አቅርቦት እየተፈታ ዘላቂነቱ ላይ ይሰራል ያሉት ኢንጂነር ታከለ፣ መጠኑንና ሀብቱ የሚገኝበትን ቦታ በባለሙያዎችና በአማካሪዎች በጥናት ለመለየት ሥራዎች መጀመራቸውንም አስታውቀዋል። በዚህ ላይ መንግሥት፣ አምራቾች፣ኩባንያዎችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ያላቸው ሚና ተወስኖ ወደልማቱ የሚገባበት ሁኔታ እንደሚመቻችም ገልጸዋል።

ይህ ጊዜያዊና ዘላቂ የመፍትሄ አቅጣጫ እርምጃ በግንባታው ዘርፍ ላይ የሚስተዋለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት፣ ለብረት ግብአትና ብረት ግዥ በከፍተኛ ደረጃ የሚወጣውን የአገር መዋእለ ነዋይ፤ለማዳን እንደሚረዳ ጠቅሰው፣ ለዜጎች የሥራ እድል የመፍጠር ሚናውም ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የብረት ኢንዱስትሪ በቀላሉ የሚታሰብ እንዳልሆነና አንድ ትልቅ መንደር ወይም ወረዳን ያህል ተደርጎ እንደሚወሰድ የተናገሩት ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ የሚገኙት የብረት ኢንዱስትሪዎች ወይንም ፋብሪካዎች የሚያመርቱት መጠንም ሆነ የሚጠቀሙት ቴክኖሎጂ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ይላሉ።

120 ሚሊየን ህዝብ ላላት ትልቅ ኢትዮጵያ፣ የብረት ኢንዱስትሪው በመንግሥት ደረጃ ካልተመራ በስተቀር የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ብቻ ስኬታማ መሆን እንደማይቻልም አስገነዝበዋል። የማዕድን ፖሊሲውም ይህንኑ አቅጣጫ ማስቀመጡን ነው ያመለከቱት።

የብረት ማእድን ክምችት በአማራ ክልል ሰቆጣ፣ በምዕራብ ኦሮሚያ፣ ደቡብና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚገኙ የሚያመለክቱ መረጃዎች መኖራ ቸውንም አስታውቀዋል።ጉዳዩ የክምችት አይደለም ያሉት ሚኒስትሩ፣ እንደ አገር ለዘርፉ ትኩረት አለመ ሰጠቱን ከዋና ዋና ችግሮቹ አንዱ አድርገው ይጠቅሳሉ።

‹‹ትኩረት ሁሉ ከውጭ በሚገባ ግብአት ላይ ነው የነበረው።እንደ አለመታደል ሆኖ ኢትዮጵያ የሸቀጦች ማራገፊያ ሆና ነው የቆየችው፡፡›› ያሉት ኢንጂነር ታከለ፣ ያም ሆነ ይህ በዚህ ወቅት መንግሥት ለመሥራት በእቅድ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ከግንባታ ግብአት አቅርቦት አንዱ በሆነው ብረት ላይ ነው›› ሲሉም ያለፉ ችግሮች አሁን ላይ ያስከተሉትን ክፍተቶች አመልክተዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ የብረት ኢንዱስትሪን ለመምራት ቤተሙከራ (ላብራቶሪ)ማሟላት ወሳኝ ነው። ከዚህ አኳያ ከሞላ ጎደልም ቢሆን የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ኢኒስቲትዩት ላብራቶሪ አለው፡፡ ያለውን ማደራጀት፣ በቴክኖሎጂና በሰለጠነ የሰው ኃይል ብቃቱን በማሳደግ እውቅና መስጠት ይጠበቃል፡፡

ብረትን ለማስመርመር ናሙና ወደ ውጭ መላክ ይጠበቃል። በዚህ ወቅትም የተለያየ ወጪዎችን ማውጣት ይጠበቃል።ለምርመራ የተላከው ብረት ትክክለኛ መረጃ ማገኘት ላይም የራሱ ክፍተት አለው።ለምርመራ የሚላክብቻው አገሮች ግብአቱን መልሰው በግዥ የሚረከቡ በመሆናቸው ጥራት አለው ለማለት የሚደፍሩበት ሁኔታ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከትና የጥቅም ግጭትም የሚያስከትል ሆኖ የሚገኝባቸው አጋጣሚዎች የበዙ ናቸው።

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ኢንስቲትዩትን በተሻለ አደረጃጀት ማጠናከር የተፈለገው እነዚህን ሁሉ ክፍተቶች ለመሙላት ወይንም ለማስቀረት ነው። ኢንስቲትዩቱን በሰው ኃይል ለማደራጀት እየተደረገ ያለው ጥረት በቅርቡ ይጠናቀቃል። በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ካላቸው ድርጅቶች ጋር ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

እንዲህ ያለው እንቅስቃሴ ኢንስቲትዩቱን በቴክኖሎጂ ለማደራጀት ብቻ ሳይሆን፣ በቤተሙከራ ውስጥ የሚያከናወነውን የብረት ናሙና ፍተሻ ስራዎች ለማስተካከል ጭምር ይጠቅማል።ከዚህ ቀደም ለፍተሻ ተብሎ ከመሬት ውስጥ ይወሰድ የነበረው ናሙና በቂ አልነበረም። ናሙናው በጥልቀት ከተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ መወሰድ ይኖርበታል።

የኢኮኖሚና የአዋጭነት ጥናት የሚያካሂድ፣ በአጠቃላይ አማራጭ የሆኑ ኢንዱስትሪውን ወደ አንድ ደረጃ የሚያደርስ ሥራ በመንግሥት እየተሰራ ይገኛል። ይህም በሶስትዮሽ የሚከናወን ተግባር ነው። መንግሥት ዋናው ሲሆን፣ አምራች ኢንዱስትሪዎችና በቴክኖሎጂው በቂ እውቀት ያላቸው ኩባንያዎች ባለድርሻ ናቸው። ማዕድን ሚኒስቴር በግንባታው ዘርፍ ከተሰጠው አንዱ ተልእኮ የብረት ማዕድን ላይ እንደሆነና በዚህ ረገድም የሚጠበቅበትን ለመወጣት ጥረት እያደረገ መሆኑን ሚኒስትሩ አስረድተዋል፡፡ ከንግግር ባለፈ ተግባር ይቀድማልም ብለዋል፡፡

በአጭር ጊዜና በዘላቂነት በመንግሥት የተጀመረው የመፍትሄ እርምጃ እንደተባለው በክትትልና በቁጥጥር ከተተገበረ በዘርፉ ላይ የሚስተዋለውን የግብአት እጥረት በመፍታት የተጓተቱ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ እንዲሁም አጋጣሚን ተገን በማድረግ በመካከል ላይ ሆነው ያልደከሙበትን ለማግኘት የሚሯሯጡት አንዳንድ ኃይሎች ከሰንሰለቱ ማስወጣት ይቻላል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## አባ ጎሹ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)**

ድስት ጠጋኙ አባ ጎሹ የአይኖቻቸውን እዳሪ በእጃቸው እያባበሱ የማለዳዋን ጀምበር ተከትለው ከቤት ወጡ።ለአንድም ቀን ከጎባጣ ጀርባቸው ላይ ወርዶ የማያውቀው አሮጌ ማዳበሪያ በስብርባሪ ብረታ ብረት ተሞልቶ ዛሬም እንደታዘለ ነው።የሁልጊዜም ጸሎታቸው የማዕድ ቤት ድስቶች ሁሉ ተሸንቁረው እሳቸውን እንዲጠብቁ ነው፡፡

አባ ጎሹ ቀይ ናቸው።ቀይነታቸው ግን አይታይም። ወይቧል። በውብ የሽማግሌ ፊታቸው ላይ እድሜ የተጫነው የደስ ደስ ይታያል። የእድሜያቸውን አሀዝ ባያውቁትም በነሉሲ ዘመን እንደነበሩ ግን ገጻቸው ምስክር ነበር። ቁመታቸው ረጅም ነው... ከለግላጋነታቸው የተነሳ ከእግዜር ጋር በቅርበት የሚነጋገሩ ብቸኛው ፍጡር አስመስሏቸዋል። የሰፈራቸውን አቧራማ መንገድ ጨርሰው .... ራቅ ካለ መንደር ደረሱ።.......ከጎዳናው ግራና ቀኝ ካለው ቤት ላይ አይኖቻቸውን እያንቀዋለሉ

“ቀዳዳ ድስት ያለው.. ቀዳዳ ድስት ያለው.. አሮጌ ድስት አዳሹ መጥቷል አባ ጎሹ። እያሉ ከአንዱ ሰፈር ወደ አንዱ ሰፈር ኳተኑ። እሳቸው የእለት ጎርሳቸውን የሚሸፍኑበትን አንድም የጥገና ስራ ሣያገኙ አብራቸው የወጣችው የማለዳ ጀንበር ጥላቸው ሸሸች።አባ ጎሹ በየመንገዱ የሚያገኙትን የሰው ቤት በቅልውጥና እያማተሩ” ቀዳዳ ድስት ያለው ..... ሰባራ ድስት ያለው አሮጌ ድስት አዳሹ መጥቷል አባ ጎሹ።በማለት እንደ እድር ለፋፊ ጉሮሮአቸው እስኪንጣጣ ጮሁ።ይህ የራሳቸው ግጥም ነው..... በእድሜ የተማሩት ..... በዘመን ያጠኑት የእንጀራ ገመድ።የደንበኞቻቸውን ቀልብ ለመሳብ የዘየዱት መላ፡፡

በሰፈሩ ውስጥ ድስትና ወይዘሮ የሌለ እስኪመስል ድረስ ጥሪያቸውን የሰማ አንድም ሰው አልነበረም።ሆዳቸውም መራቡን ሊያስታውቅ እንደ ሰኔ ሰማይ አጉረመረመ።እውነት ለመናገር የዘመናቸውን ገሚሱን ያሳለፉት በጾም ነው።ሁሉም ቀን ለእሳቸው የጾም ቀን ነው።...የድህነት ጾም።አሁንም አልበሉም።ትላንት የባቄላ አሹቅ እንደቀመሱ ነው።ሁሌም ጾመኛ ሁሌም ምኞተኛ ናቸው.... ሽማግሌው አባ ጎሹ፡፡

በአዋጃቸው መሃል አንድ የተስፋ ድምጽ ሰሙ።አንዲት ወይዘሮ ሴት «ወዲህ ይግቡ» ስትል ጠራቻቸው። ከመግባታቸው ወስፋት የሚቀሰቅስ የምግብ ሽታ ተቀበላቸው።በአምሮት ወስፋታቸው ተንጫጫ፡፡

ወይዘሮዋ ከወደማዕድ ቤት በኩል ሁለት እኩል መጠን ያላቸውን መናኛ ድስቶች ይዛ ተመለሰች፡፡

“ይሄውሎት በደንብ አድርገው ይስሩት” ስትል አቀበለቻቸው።ብዙም ጎልማሳነት ባልሸሻቸው አይኖቿ ስታያቸው ቆይታ ካጠገባቸው እብስ አለች። ስትራመድ ዳሌዋ ይደንሳል..... ወጣትነት ከድቶት በጉልምስና እድሜ ላይ ቢሆንም ወንድ ልጅ ለማነሁለል ሀይል ነበረው፡፡

አባ ጎሹ ሁለቱን ድስቶች አገላብጠው ካዩ በኋላ ከማዳበሪያው ውስጥ መዶሻና መጠገኛ ብረት በማውጣት መቀጥቀጥ ጀመሩ።ቀጥቅጠው ካቆነጇቸው መንትያ ድስቶች የሚያገኟትን አስር ብር በምን እንደሚያጠፏት በልባቸው እቅድ ጀመሩ።እንዲህ በደከማቸውና ሕይወት ባስመረረቻቸው ሰዓት የመጠጣት... ጠጥቶም የመስከር አመል አለባቸው። በዚህም በሚያገኟት አስር ብር ሊጎነጬ እቅድ ያዙ። ቀጥቅጠው ያሳመሩትን አሮጌ ድስት ለወይዘሮዋ ሊሰጡ... ድምጽ አሰሙ ......... እሜቴ የሚል፡፡

የጥሪ ድምጽ የሰማቻቸው ወይዘሮ ከለስላሳ ጸጉሯ ላይ የተንሸራተተ ሻሽዋን በእጀቿ እያጠበቀች ወደ ውጪ ወጣች።

“ይሄውልሽ ኩችም አድርጌ አበጅቼልሻለሁ። የፈለግሽውን ነገር ልታበስይበት ትችያለሽ” ሲሉ አቀበሏት።

ወይዘሮዋ የድስቶቹን ቂጥና ሆድ ካየች በኋላ ስንት ነው? ስትል ጠየቀች፡፡

‹አስር ብር ይበቃኛል› መለሱላት፡፡

በሻሿ ጠቅልላ ጆሮ ግንዷ ስር የደበቀችውን አስር ብር አውጥታ ሰጠቻቸው፡፡

አባ ጎሹ ብርቅ የሆነችባቸውን አስር ብር ሰባት ጊዜ አጣጥፈው ከሱሪያቸው ስር ካለ ሌላ ኪስ ውስጥ በመክተት ወይዘሮዋን አመስግነው ሄዱ።ቀዳዳ ድስት ያለው፣ አሮጌ ድስት አዳሹ መጥቷል አባ ጎሹ ከማለታቸው ከወጡበት ቤት ቀጥሎ ካለው ሶስተኛው ግቢ ውስጥ ጥሪ ሰምተው ወደዛው አመሩ።የጎረቤት ሰዎች እርስ በእርስ እየተጠራሩ ለአባ ጎሹ የገቢ ምንጭ ሆኑ።ጀምበር ከጠለቀች ጀምሮ አባ ጎሹ አምስት አሮጌ ድስቶችን አደሱ።እንዳሰቡት ርሀብና ድካማቸውን ሊረሱ ቀን ሙሉ ተንከራተው ያገኟትን ሃያ አምስት ብር ጨብጠው ብረት የሞላውን አሮጌ ማዳበሪያ እንደተሸከሙ ወደ መሸታ ቤት አቀኑ። ገና በር ከመድረሳቸው የአረቄው ሽታ ሰነፈጣቸው። የጀርባቸውን ሸክም ሰዋራ ቦታ ደብቀው ወደ ውስጥ ገቡ። ሃያ አምስት ብሯን ዳግመኛ ቆጥረው ለማውጣት እንዲመቻቸው በማሰብ ከደረት ኪሳቸው ውስጥ ከተቱት፡፡

ከፊት ለፊታቸው አንድ ወጣት ጨለምለም ካለ ቦታ ላይ ተቀምጦ እያያቸው እንደሆነ አልተረዱም ነበር።ወጣቱ የጎፈረ ጸጉሩን በእጁ እያፍተለተለ የአባ ጎሹን ሃያ አምስት ብር እንዴት መውሰድ እንዳለበት ሲያሰላስል ነበር፡፡

አባ ጎሹ ገና ቂጣቸው መሬት ከመንካቱ አረቄ አዘዙ። የናፈቁትን መጠጥ በአንድ ትንፋሽ ጨለጡት። ሆዳቸው ቅጥል፣ አንጀታቸው እርር አለ።ደግመው ጠረጴዛውን ቆረቆሩ እስከ አፍጢሙ ተሞላላቸው።አባ ጎሹ ያለወትሯቸው ቶሎ ሰከሩ።ደክመው የለ?......ተርበው የለ?

ወጣቱ ከዚህ በላይ ጊዜ ማጥፋት አልፈለገም።የአባ ጎሹ ስካር የፈለገውን እንዲያደርግ እድል ስለሰጠው ከተቀመጠበት ተነሳ።በዘየደው መላ የደረት ኪሳቸውን ፍራንክ ሊወስድባቸው የቅርብ ዘመዱን ያገኘ ያህል ደስ በሚል ፈገግታ ተንደርድሮ አቀፋቸው ።‹እንዴት ኖት?.....ሰላም ኖት ? ጠፉ እኮ.. በሰላም ነው ? ሰላምታው ማብቂያ አልነበረውም።ወጣት ትከሻውን ስንት ነገር የተሸከመ አዛውንት ትከሻቸው ላይ እያጋጨ የሰላምታ መአት አወረደባቸው፡፡

አባ ጎሹ በወጣቱ ሰላምታ ተደስተው አቅፈው አገላብጠው ሳሙት።ቢያውቀኝ ነው እንጂ በሚል የደግነት ስሜት ሣያውቁት አጻፋቸውን መለሱለት፡፡

ወጣቱ እንዳሰበው የአባ ጎሹን ሃያ አምስት ብር ከደረት ኪሳቸው ውስጥ ሞጭልፎ ተሰወረ። ደማቸውን፣ የሽማግሌ ወዘናቸውን ነጥቆ እብስ አለ።አባ ጎሹ አገር ሰላም ብለው አረቄያቸውን ይኮመኩማሉ። በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ፣ ሌላ ሙልት እሱንም ፉት.. ጭልጥ.. ጠረጴዛ መቆርቆር።አፍና ብርጭቆአቸው ሳይለያይ ሰዓቱ ነጎደ።ፈጣኖቹ አስተናጋጅ ከአባ ጎሹ ፊት ሣይሸሹ በአፍ..በአፉ ይሞሉላቸዋል።አባ ጎሹ የደረታቸውን ሃያ አምስት ብር ተማምነው ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ጠጡ።

# ዓለም አቀፍ




## በሱዳን በመሬት ግጭት የ15 ሰዎች ሕይወት ጠፍቷል

በሱዳን በብሉ ናይል ግዛት በመሬት ይግባኛል የተነሳው ግጭት በመባባሱ ቢያንስ 15 ሰዎች መገደላቸውን የዓይን እማኞች እና የአገሪቱ ጤና ጥበቃ ባለስልጣናት አስታወቁ።

ግጭቱ የተቀሰቀሰው ከዋና ከተማው ካርቱም በስተደቡብ 500 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ዋድ አል-ማሂ በምትባል ትንሽዬ ከተማ ሲሆን በመሬት ይገባኛል ሳቢያ በሐውዜን አባላት እና በተቀናቃኝ ቡድኖች መካከል መሆኑ ቢቢሲ ዘግቧል።

በወቅቱ በአካባቢው ከፍተኛ የተኩስ ድምጽ መስማታቸውንና የተቃጠሉ መኖሪያ ቤቶችን ማየታቸው ነዋሪዎቹ መግለጻቸውን በዘገባው ተጠቅሷል።በተመሳሳይ መልኩ በከተማው የሚገኘው የአንድ ክሊኒክ ሰራተኞች በርካታ አስከሬኖች ወደ ክሊኒካቸው መምጣቱንም አስታውቀዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በብሉ ናይል ግዛት በአካባቢው በጎሳዎች መካከል በተፈጠረው የመሬት ግጭት 64 ሰዎች ሲገደሉና በመቶዎች የሚቆጠሩት መቁሰላቸው ይታወሳል።በወቅቱ በርካታ መኖሪያ ቤቶች ሲቃጠሉ የመንግስት ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል።በዚህ ምክንያት የአገሪቱ መንግስት በርካታ የጸጥታ አካላት ወደ አካባቢው በማሰማራት የሰዓት እላፊ ገደብ ለመጣል ተገዶ እንደ ነበርም ተነግሯል።


የግጭቱ መንስኤዎች ብዙ ቢሆኑም በዋናነት ግን የሃውሳ ጎሳዎች በብሉ ናይል ክልላዊ አስተዳደር ውስጥ ለመካተት በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ነው።የጎሳውን ጉዳይ በተገቢው ለሚመለከተው አካል የሚያቀርብ መሪ በመመረጡ ጋር ተያይዞ ከአካባቢው ገኘ ተቃውሞ ገጥሟቸው ነበር፡፡

የሃውሳ ጎሳዎች በግዛቱ የሚወክላቸው የራሳቸውን መሪ መምረጣቸውን ተከትሎ በኢትዮጵያ ድንበር አቅራቢያ በምትገኝ በበካይሳን ከተማ፣ በሃውሳ ጎሳ አርሶ አደሮች እና በበርታ ጎሳ እረኞች መካከል ባሳለፍነው ወርሃ ሐምሌ በተፈጠረው ግጭት ከሁሉቱም ጎሳዎች በርካታ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል።

## በኬንያ በተከሰተው የኮሌራ ወረርሽኝ ትልቅ ሥጋት ፈጥሯል

በኬንያ በስድስት ወረዳዎች በተከሰተው የኮሌራ ወረርሽኝ እስካሁን 61 ሰዎች መያዛቸው የአገሪቱ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መግለጹን ቢቢሲ አስነብቧል።

በአገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ የወረርሽኙን ስርጭት ያባብሳል ተብሎ ትልቅ ስጋት ፈጥሯል።እንደ ዘገባው ከሆነ በወረርሽኙ ከተያዙት ሰዎች 13ቱ በሆስፒታል ህክምና እየተደረገላቸው ሲሆን 40 የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት እየተደረገላቸው ይገኛል።ስምንት የሚሆኑት ሕሙማን ግን በተደረገላቸው ህክምና ድነው ከሆስፒታል መውጣታቸው ተነግሯል፡፡



ወረርሽኙ የተከሰተው በአብዛኛው ማለትም 48 የሚሆኑ በበሽታው የተያዙ ሰዎች በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ እና አጎራባች ኪያምቡ ካውንቲ ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ በስምጥ ቫሊ አውራጃዎች ናኩሩ፣ ካጂዶ እና ኡሲን ጊሹ፣ እና አንድ ጉዳይ በማዕከላዊ ሙራንጋ ካውንቲ መሆኑ ታውቋል።

ሚኒስቴሩ ወረርሽኙን ለመከላከል ወረርሽኙ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ባለሙያዎቹን የላከ ሲሆን የድርቁ ሁኔታ ግን አሁንም ሥጋት ሆኗል፡፡

ለመሆኑ በኬንያ የሚከሰት የኮሌራ ወረርሽኝ አዝማሚያ እንዴት ይገለጻል?

ከ panafrican-med-journal.com የተገኘው መረጃ በኬንያ በዘመናት መካከል የተከሰተው የኮሌራ ወረርሽኝ ሁኔታ ምን እንደሚመስል በደንብ አብራርቷል።ኬንያ የካኩማ፣ ካሎቤዬይ እና ዳዳብ ታዋቂው የስደተኛ ካምፖች ባለቤት ናት።ካኩማና ካሎቤዬይ ካምፖች በሰሜን-ምዕራብ ኬንያ በቱርካና ግዛት ውስጥ ይገኛሉ።ግዛቱ በበረሃ እና ከፊል-በረሃ በሆነ አየር ንብረት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በየአምስት ዓመት በከባድ ድርቅ የሚጠቃ ግዛት ነው፡፡

በሁለቱ ካምፖች ከሱዳን፣ ከሶማሊያ፣ ከቡሩንዲ፣ ዩጋንዳ፣ ከሩዋንዳ፣ ከኤርትራ፣ ከኮንግ እና ከኢትዮጵያ የሚመጡ ስደተኞችን ያስተናግዳሉ።የቱርካና ግዛት ከኬንያ ግዛቶች የመጨረሻ ድሃ ሲሆን በግዛቱ ከሚኖሩት ሰዎች 79 በመቶዎቹ ድሆች ናቸው።በስደተኞችና የግዛቱ አርብቶ አደሮች መካከል በብዙ መልኩ የጠበቀ ግንኙነት በመኖሩ ብዙውን ጊዜ ለወረርሽኝ መስፋፋትና ተጋለጭነት ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

እ.ኤ.አ በ2005 በካኩማ የስደተኞች ካምፕ በተቀሰቀሰው የኮሌራ ወረርሽኝ 418 ሰዎች በበሽታው ሲጠቁ ከእነዚህ አራት ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል።በተመሳሳይ መልኩ በ2009 በተቀሰቀሰው የኮሌራ ወረርሽኝ 224 ሰዎች ሲያዙ አሁን አራት ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል።በ2015 በኬንያው የዳዳብ ስደተኞች ካምፕ በተከሰተው አደገኛ የኮሌራ ወረርሽኝ ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎች ሲጠቁ፣ በአሥር ሰዎች ላይ የሞት ጉዳት አድርሷል።

ወረርሽኙ እ.ኤ.አ በ2017 ብቻ በኬንያ ለ76 ሰዎች ሞት ምክንያት ሲሆን የበሽታው ስርጭት ወደ 2 በመቶ ከፍ ማለቱም ተገልጿል፡፡

# ስፖርት





# ኢትዮጵያውያን ያልተካተቱበት የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች ምርጫና እጩዎች

**ብርሃን ፈይሳ**

የየትኛውም አትሌት ዓላማ እና ህልም በሚወዳደርበት ርቀት በትልልቅ መድረኮች ተሳትፎ ውጤታማ መሆን ነው። አሸናፊነቱ በኦሊምፒክ እና በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና አሊያም በሌሎች ቻምፒዮናዎች ሲሆን ደግሞ ከራስ ስም በላይ አገርንም የሚያኮራ በመሆኑ ክብሩ ድርብ ይሆናል። ከሁሉም የሚልቀው ግን የአትሌቱ አሸናፊነት በዓለም ደረጃ እውቅና አግኝቶ የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሲሰኝ ነው። ይህ እድል ደግሞ ብዙዎቹ የሚቀዳጁት ሳይሆን እጅግ ጠንካራዎች የሚያሳኩት ነው።

ዓለምን ባስደመሙ ምርጥ አትሌቶቿ የምትታወቀው የሯጮቹ ምድር ኢትዮጵያም በተካፈሉበት ውድድሮች ብቻም ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ቁጥር አንድ የተሰኙ አትሌቶቸ በርካታ ናቸው። እአአ ከ1988 ጀምሮ በየዓመቱ በዓለም አትሌቲክስ አማካኝነት የሚያካሂደውንና በአትሌቲክስ ቤተሰቡ ድምጽ የሚሰጥበትን የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሽልማት ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል። በኢትዮጵያውያን አትሌቶች ረገድ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ሽልማት አሸናፊ የሆነው ጀግናው ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ነው። አትሌቱ አሸናፊ የሆነበት ውድድር ደግሞ እአአ በ1998ቱ ነው። እአአ በ2004 እና 2005 ደግሞ ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ በተከታታይ አሸናፊ በመሆን ታሪካዊ አትሌትነቱን አረጋግጧል።

በሴቶች በኩል እአአ በ2007 ምርጥ አትሌት የተባለችው አትሌት መሰረት ደፋር ነበረች። እአአ በ2015 እና 2016 ደግሞ ገንዘቤ ዲባባ እና አልማዝ አያና የምርጥ አትሌትነት ምርጫው ኢትዮጵያ ላይ እንዲያርፍ ያደረጉ አትሌቶች ናቸው። ዘግይቶ በተጀመረው የምርጥ ተስፈኛ አትሌቶች ምርጫም ወጣቱ አትሌት ሰለሞን ባረጋ እአአ



በ2019 ተሸላሚ ለመሆን ችሎ ነበር። ይሁንና ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አሸናፊዎች ብቻም ሳይሆን እጩ ውስጥ የመግባት እድላቸው እየተመናመነ ሲሄድ ታይቷል። የዘንድሮው ዓመት (2022) የምርጥ አትሌቶች ዝርዝር ላይም 20 አትሌቶች በእጩነት በሁለቱም ጾታ ቀርበዋል። ይሁንና በዝርዝሮቹ ውስጥ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አልተካተቱም። ይህም አትሌቲክስ መታወቂያዋ ከሆነው ኢትዮጵያ ብዙዎች የሚጠብቁት አይደለም።

እየተገባደደ በሚገኘው የፈረንጆቹ ዓመት ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ የተሻለ ስኬታማ የሚባል ነበር። ምክንያቱ ደግሞ በዓመቱ ከተካሄዱት ታላላቅ ቻምፒዮናዎች ማለትም የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና እንዲሁም በአሜሪካዋ ኦሪጎን የተደረገው የአትሌቲክስ ዓለም ቻምፒዮና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በመሪነት በማጠናቀቁ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በርካታ አትሌቶች በዳይመንድ ሊጎች እና ሌሎች የግል ውድድሮች ላይ በመካፈል እንደተለመደው ውጤታማ ዓመት ነበር ያሳለፉት። የዓለም አትሌቲክስ እጩዎቹን ይፉ ሲያደርግም በዓመቱ ዋና ዋና በሚባሉ ውድድሮች ላይ ያስመዘገቡትን ውጤት መሰረት በማድረግ ነው። ታዲያ በእነዚህ ቻምፒዮናዎች ስኬታማ የነበሩት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ለምን ሳይካተቱ ቀሩ የሚለው ጥያቄ የበርካቶች ነው።

ለአብነት ያህል በቤልግሬድ በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ ከዓለም አንደኛ በመሆን ነበር ያጠናቀቀችው። ከተመዘገቡት የወርቅ ሜዳሊያዎች መካከልም አንድ ሜዳሊያ በአትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ነበር የተገኘው። አትሌቷ ከወራት በኋላ በተካሄደውና ኢትዮጵያ ከዓለም ሁለተኛ በሆነችበት የኦሪጎኑ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ደግሞ በ5ሺ ሜትር የወርቅ እንዲሁም በ1ሺ500 ሜትር የብር ሜዳሊያዎችን ነበር ያጠለቀችው። አትሌቷ በሌቪን እንዲሁም በቤት ውስጥ የቱር ውድድር ድንቅ ብቃቷን ያሳየችበት የዓመቱ ውድድር ነበር። ዳመንድ ሊግ ላይም እስከመጨረሻው መጓዝ የቻለችና ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት ሲሰጣት የቆየችም አትሌት ናት። ይሁንና ይህቺ አትሌት ከእጩዎቹ አንዷ ልትሆን አልቻለችም።

ይህ ጉዳይ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይም የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች ምርጫ ዝርዝር ውስጥ የሚካፈሉ አትሌቶች፤ በአትሌቲክስ ማለትም ረጅም፣ መካከለኛ እና አጭር ርቀት የመም፣ የሜዳ ተግባራት እንዲሁም የጎዳና ላይ ሩጫ ላይ የተካፈሉ አትሌቶች ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ እየታየ ያለው በእጩነት ከሚቀርቡት አትሌቶች መካከል አብዛኛዎቹ የአጭር እና መካከለኛ ርቀት አትሌቶች እንዲሁም የሜዳ ተግባራት አትሌቶች ናቸው። የረጅም ርቀት የመም አትሌቶች በምርጫው እምብዛም የማይካተቱ ሲሆን፤ ጥቂት የጎዳና ላይ ሯጮች ብቻ በእጩነት ውስጥ እንደሚገቡ በግልጽ የሚታይ ነው። ይህ ደግሞ ምዕራባዊያን ለራሳቸው ከሚሰጡት ስፍራ የተነሳ ሊሆን እንደሚችል ብዙዎች ይስማማሉ።


## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የ8ኛ ዕዝ ለ2015 በጀት ዓመት ለክፍሉ አገልግሎት የሚውል አላቂ የጽህፈት መሳሪያዎች፤ የተለያዩ የቢሮ እቃዎች፣ አላቂ የጽዳት ዕቃዎችን፣ የኤሌክትሮኒክስና ኤሌክትሪክ ዕቃዎችን፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎችን፣ ጀኔሬተርና የጀኔሬተር መለዋወጫዎችን፣ የጥገና አላቂ ዕቃዎችን፣ የኮምፕ ጥገና /የግንባታ/ ዕቃዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ የእቃ ግዥው መለያ ቁጥር መከ/8ኛ ዕዝ/ግ/ጨ/01/2015 ሲሆን የመንግሥትን ግዥ መስፈርቶች የሚያሟሉ እና በዘርፉ ከተሰማሩ ህጋዊ ድርጅቶችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ተጫራቾች አግባብ ያለው የዘመኑን ግብር የተከፈለበት እና የታደሰ ንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ የሚችሉ፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አቅራቢዎች ዝርዝር ሊስት ላይ የተመዘገቡና በጨረታ ላይ መሳተፍ የሚያስችል ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ካደራጃቸው አካል ህጋዊ የትብብር ደብዳቤ ይዞ መምጣት ይጠበቅባቸዋል። ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ ከሚያቀርበው ጠቅላላ ዋጋ 2% ማቅረብ ይኖርበታል። ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ 15 ቀናት በኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ህንፃ ፊት ለፊት ባለው ህንፃ ቢሮ ቁጥር 11 ግዥ ክፍል በመቅረብ የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ ለተዘጋጀው ሰነድ ክፍያ ፈጽመው ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡ ሲፒኦ ሲዘጋጅ በመከላከያ ሚኒስቴር ለ8ኛ ዕዝ በሚል ስም ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ሳምፕል ለሚያስፈልጋቸው እቃዎች ሳምፕል ማቅረብ ይጠበቃል፡፡ ተጫራቾች ለሚያቀርቧቸው እቃዎች ዶክሜንቶችን ፋይናንሻልና ቴክኒካል እንዲሁም ኦርጅናል እና ኮፒ ለየብቻው በተለያዩ ፖስታ በታሸገ ኤንቨሎፕ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ እስከ 11/02/2015 ዓ.ም በደቡብ ወሎ ዞን ኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 161 ከተማ አስተዳደር ህንፃ ፊት ለፊት ባለው ህንፃ ቢሮ ቁጥር 11 ግዥ ክፍል ዘወትር በሥራ ሰዓት መውሰድና ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡፡ ጨረታው 25/02/2015 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ላይ የጨረታ ሳጥኑ ታሽጎ በዕለቱ 8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ለዚሁ በተዘጋጀ ቢሮ በግልጽ ይከፈታል፡፡ ክፍሉ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር፡- 0911505133 ወይም 0912727203 መደወል ይችላሉ፡፡**

**በኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር የ8ኛ ዕዝ ኮምቦልቻ**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## ቁጥር ECWCT NCB/PG/44/2015

1. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በትራንስፖርት መሠረተ ልማት ዘርፍ ስር ለሚገኙት የደብረማርቆስ አየር ማረፊያ ዲዛይን ግንባታ ፕሮጀክት እና ቡታጅራ ከተማ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መ/ግ/ፕሮጀክት ቤዝኮርስ፤ለአስፋልትና ለኮንክሪት ሥራ የሚውል የተፈጨ ጠጠር በማስፈለጉ በሀገር አቀፍ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ተጫራቾችን ይጋብዛል፡፡
2. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን የዘመኑን ግብር የከፈሉበት ከሚፈለገው አገልግሎት ጋር የተዛመደ የ2015 ዓ.ም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ መሆናቸውን ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እና በጨረታው ለመሳተፍ ከሚመለከተው ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ በማቅረብ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ዘወትር በሥራ ሰዓት የማይመለስ ብር 300.00 /ሦስት መቶ ብር/ በመክፈል ዋና መ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኘው በግዥ መምሪያ ሁለት ቢሮ በመቅረብ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ መግዛት ይችላሉ።
3. የጨረታው አሸናፊ የሚሆነው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተመለከቱት መስፈርቶች መሠረት ሲሆን ጨረታው ዜግነትን ሳይመለከት ለማንኛውም አቅራቢ ክፍት ነው፡፡ የጨረታ ሰነዱ የተዘጋጀው በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡
4. አቅራቢዎች የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን ለዚህ ተግባር በተዘጋጀ ሳጥን በግዥ መምሪያ ቢሮ ገቢ የሚያደርጉበት የመጨረሻ ቀን ጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ከሰዓት 9:00 ድረስ ብቻ ነው።
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይንም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም. ከሰዓት 9:30 ጉርድ ሾላ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ህንፃ 200 ሜትር ገባ ብሎ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ቅጥር ግቢ በግዥ መምሪያ ቢሮ ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች ለሚያቀርቡት ዕቃ ለሎት1 ብር 270,000.00፤ ለሎት 2 ብር 30,000.00 እና ለሎት 3 ብር 200,000.00 የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ (CPO) ወይም በባንክ ዋስትና /Bank Guarantee/ ከጨረታ ሰነድ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ በቼክ፣ በጥሬ ገንዘብ፣ በኢንሹራንስ ወይም በሌላ መልክ የሚቀርብ የጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡
7. ተጫራቾች በጨረታው ደንብና መመሪያ መሠረት የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፤ ከጨረታው ደንብና መመሪያ ውጪ የሚቀርብ ማንኛውም ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
8. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
9. ለበለጠ መረጃ ተጫራቾች የሚከተለውን አድራሻ መጠቀም ይችላሉ፡፡

**የፖስታ ሣጥን ቁጥር ፡-21952/1000**
**የስልክ ቁጥር፡- 0118 96 29 91/ 011 872 30 86**
**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

**የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን**